
ከድኅነት ወደ ልማት:- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ
2ኛ ዙር ተከታታይ ዕትም፣ ቁጥር 1

*ተካ ኤገኖ*

# አንጋፋው የኢንቨስትመንትና የግሉ ክፍለ-ኤኮኖሚ ተዋናይ



የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ)



ከድህነት ወደ ልማት፡- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ
2ኛ ዙር፡ ተከታታይ ዕትም፣ ቁጥር 1

*ተካ ሌገኖ*

# አንጋፋው የኢንቨስትመንትና የግሉ ክፍለ-ኤኮኖሚ ተዋናይ

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ
አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ የታተመ

**አድራሻ፡**

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ
ፖ.ሣ.ቁ. 25864 ኮድ 1000
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ስልክ፡ (251-11) 157-2990/91
ፋክስ፡ (251-11) 157-2979
ኢ.ሜይል: fss@ethionet.et
ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org.et

© 1999 የማኅበራዊ ጥናት መድረክ

የሽፋንና የገጽ ዲዛይን፡- በምህረት ደምሰው

ISBN 99944-50-09-3

ይህ ጽሑፍ የታተመው ከኖርዌይ ኤምባሲ፣ ከኔዘርላንድስ ኤምባሲ፣ ከአየርላንድ ኤምባሲና ከእንግሊዝ ዓለም-አቀፍ የተራድዖ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው።

በዚህ ሕትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የማጥመን፣ የሥራ አመራር ቦርዱን ወይም የማጥመን አጋሮች አመለካከት ሳያንፀባርቁ ይችላሉ።

## ማውጫ

**መግቢያ**
*ሺፈራው በቀለ*................................................................................................ *i*

**የመክፈቻ ንግግር**
*ፕ/ር ባሕሩ ዘውዴ*........................................................................................... *iii*

**የቀኛዝማች ተካ ኤገኖ አጭር የሕይወት ታሪክ**.................................................1
*መኮንን ተገኝ*

**በውይይት ወቅት የቀረቡ ጥያቄዎችና አስተያየቶች**...........................................21

# FSS Publications List

**[currently available in stock]**

| FSS Periodical |
|---|
| • *Medrek, now renamed FSS BULLETIN* (Quarterly since 1998. English and Amharic) |
| • *Africa Review of Books* (Managed by FSS for CODESRIA)<br>o Vol. 1, No. 1 (October 2004)<br>o Vol. 1, No. 2 (September 2005)<br>o Vol. 2, No. 1 (March 2006)<br>o Vol. 2, No. 2 (September 2006) |

| FSS Discussion Papers | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 5 | *Land Redistribution and Female-Headed Households: A Study in Two Rural Communities in Northwest Ethiopia.* Yigremew Adal. 2001 | 20.00 |
| No. 8 | *Livelihood Insecurity Among Urban Households in Ethiopia.* Dessalegn Rahmato and Aklilu Kidanu. 2002 | 20.00 |
| No. 9 | *Rural Poverty in Ethiopia: Household Case Studies from North Shewa.* Yared Amare. 2002 | 20.00 |
| No.10 | *Rural Lands and Evolving Tenure Arrangements in Ethiopia: Issues, Evidences and Policies.* Tesfaye Teklu. 2003 | 20.00 |
| No.11 | *Resettlement in Ethiopia: The Tragedy of Population Relocation in the 1980s.* Dessalegn Rahmato. 2003 | 20.00 |
| No.12 | *Searching for Tenure Security? The Land System and New Policy Initiatives in Ethiopia.* Dessalegn Rahmato. 2004 | 20.00 |
| No.13 | *A Comparative Study of Forest Management in Eza District, Gurage Zone, Southern Ethiopia.* Tenkir Bonger. 2005 | 20.00 |

| FSS Monograph Series | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 2 | *Poverty And The Social Context of Sex Work In Addis Ababa: An Anthropological Perspective.* Bethlehem Tekola. 2006 | 40.00 |
| No. 3 | *Democratic Assistance to Post-Conflict Ethiopia: Impact and Limitations.* Dessalegn Rahmato and Meheret Ayenew. 2004 | 25.00 |
| No. 4 | *Lord, Zega and Peasant: A Study of Property and Agrarian Relations in Rural Eastern Gojjam.* Habtamu Mengistie. *2004* | 30.00 |

| Consultation Papers on Poverty | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 3 | *Civil Society Groups and Poverty Reduction*. Abonesh H. Mariam, Zena Berhanu, and Zewdie Shitie. Edited by Meheret Ayenew. 2001 | 5.00 |
| No. 4 | *Listening to the Poor*. Oral Presentation by Gizachew Haile, Senait Zenawi, Sisay Gessesse and Martha Tadesse (in Amharic). Edited by Meheret Ayenew. 2001 | 5.00 |

| Gender Policy Dialogue Series | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 1 | *Gender and Economic Policy*. Edited by Zenebework Tadesse. 2003 | 10.00 |
| No. 2 | *Gender and Poverty* (Amharic). Edited by Zenebework Tadesse. 2003 | 10.00 |
| No. 4 | *Gender Policy Dialogue in Oromiya Region*. Edited by Eshetu Bekele. 2003 | 10.00 |
| No. 6 | *Gender Policy Dialogue in Southern Region*. Edited by Eshetu Bekele. 2004 | 10.00 |

| Consultation Papers on Environment | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No.1 | *Environment and Environmental Change in Ethiopia*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. 2003 | 10.00 |
| No.2 | *Environment, Poverty and Gender*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. 2003 | 10.00 |
| No.3 | *Environmental Conflict*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. July 2003 | 10.00 |
| No.4 | *Economic Development and Its Environmental Impact*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. 2003 | 10.00 |
| No.5 | *Government and Environmental Policy*. Consultation Papers on Environment. 2004 | 10.00 |
| No.6 | *የግልና የጋራ ጥረት ለአካባቢ ሕይወት መሻሻል (የሰሜን ሸዋ ገበሬዎች ተሞክሮ)* Consultation Papers on Environment. May 2004 | 10.00 |
| No.7 | *Environmental Challenges of Contemporary Ethiopia and the Indispensable Role of Indigenous Trees*. Legesse Negash. 2004 | 10.00 |

| FSS Studies on Poverty | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No.1 | *Some Aspects of Poverty in Ethiopia: Three Selected Papers*. Dessalegn Rahmato, Meheret Ayenew and Aklilu Kidanu. Edited by Dessalegn Rahmato. 2003 | 10.00 |
| No.2 | *Faces of Poverty: Life in Gäta, Wälo*. Harald Aspen. 2003 | 15.00 |
| No.3 | *Destitution in Rural Ethiopia*. Yared Amare. 2003 | 10.00 |

| | | |
|---|---|---|
| No.4 | *Environment, Poverty and Conflict*. Tesfaye Teklu and Tesfaye Tafesse. 2004 | 10.00 |
| No.5 | *Issues in Urban Poverty: Two Selected Papers*. Daniel Kassahun and Meron Assefa. July 2005 | 10.00 |

| **ከድህነት ወደ ልማት:- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ**<br>**From Poverty to Development: Intergenerational Transfer of Knowledge** | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| **ቁጥር 1** | ***ድርቅንና ረሀብን ለመቋቋም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች (1966-1983)::* ሽመልስ አዱኛ፣ 1997 ዓ.ም.** | 10.00 |
| **ቁጥር 2** | ***የአባይና የተፋሰሶቹ ዓለም ዓቀፋዊ ችግር::* ዘውዴ ገ/ሥላሴ፣ 1997 ዓ.ም.** | 10.00 |
| No. 2 | *The Blue Nile and Its Basins: An Issue of International Concern*. [English Version]. Zewde G/Sellassie. 2006. | 10.00 |
| **ቁጥር 3** | ***ትምህርት፣ ባህልና ዕድገት: የትዝታ ጉዞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እስከ ዓለም አቀፍ የኤኮኖሚ ተቋማት (1948-1996)::* አስፋው ዳምጤ፣ 1998 ዓ.ም.** | 10.00 |
| **ቁጥር 4** | ***ጆርናሊዝምና እድገት በኢትዮጵያ፤ የግል ትዝታዎች ከ1952 ጀምሮ::* ነጋሽ ገ/ማርያም፣ 1998 ዓ.ም.** | 10.00 |
| No. 5 | *National Air Carriers as Catalysts for Devleopment: The Case of Ethiopian Airlines (ET)*. Semret Medhane, 2006. | 10.00 |

| **Book Series** | Price (Birr) |
|---|---|
| • *Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below*. Edited by Bahru Zewde and Siegried Pausewang. Nordic African Institute, Uppsala and the Forum for Social Studies, Addis Ababa. 2006 | 80.00 |

| **Environmental Documentaries on CD and Video** | Price (Birr) |
|---|---|
| • **የከተማችን አካባቢ ከየት ወደየት?** (Amharic Video Film) | 50.00 |
| • **ውጥንቅጥ፣ ድህነትና የአካባቢያችን መጎሳቆል** (Amharic Video Film) | • 50.00 |
| • "Witinkit": Poverty and Environmental Degradation (CD in Amharic with English Subtitles) | 100.00 |

# መግቢያ

ክቡራትና ክቡራን
ውድ እንግዶቻችን

"ከድህነት ወደ ልማት፡- እውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ" በተባለው ኘሮግራም የ2[ተኛው] ዙር መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ ለመገኘትና የመጀመሪያውን ተናጋሪ ለመስማት በመገኘታችሁ በማኅበራዊ ጥናት መድረክና በራሴ ስም እንኳን ደህና መጣችሁ እላለሁ።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በዚሁ ኘሮግራም የመጀመሪያው ዙር ስምንት አንጋፋ ኢትዮጵያውያን ንግግር ማድረጋቸው ይታወቃል። እነዚህም ንግግሮች በናንተ በአድማጮቻችንና በሌሎችም ሰዎች አስተያየት ጠቃሚነታቸው ስለተረጋገጠ ማጥመ ኘሮግራሙን መልሶ ካጠና በኋላም ሌላ ዙር እንዲዘጋጅ ወሰነ። በዚህም መሠረት ሁለተኛው ዙር እንዳለፈው ሁሉ የተዋጣ ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

አሜሪካኖች "የኢንዱስትሪ አምበሎች" የሚል አገላለጽ አላቸው። ይህ በመጀመሪያ የተቀረጸው ከዛሬ መቶ ወይም መቶ ሀምሳ አመታት አካባቢ የሀገራቸው የኢንዱስትሪ አብዮት በተካሄደበት ዘመን ነበር። የኢንዱስትሪ አብዮቱ አሜሪካንን ከተራ የምዕራብ ሀገር ወደ ልዕለ ኃያል ሀገር ያሸጋገረ ክስተት ነበር። በዚህ ኢንዱስትሪ አብዮት መምጣትና መሳካት ግምባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል ተብሎ የሚታመነው ከላይ የጠቀስኳቸው "የኢንዱስትሪ አምበሎች" ነበሩ። እነዚህም እነ ጄ ፒ ሞርጋን፣ እነ አንድርው ካርኔጅ፣ ጆን ዲ ሮክፌለር፣ እና ሄንሪ ፎርድ ነበሩ። አሜሪካኖች እነዚህን ሰዎች እንደ ልዕለ ሰብዕ (Superman) ያዩዋቸዋል፤ በትምህርት ቤት የመማሪያ መጻህፍት ውስጥ አስገብተዋቸዋል፤ ስለዚህ በአብዛኛው አሜሪካዊ ይታወቃሉ፤ ወይም "የጓዳ ስሞች" ናቸው።

በብዙ ዜጐቻቸው አእምሮ ድንቂያማ ገጽታ አላቸው፤ አርአያም ተደርገዋል። ታዲያ የኢንዱስትሪ መሪዎች ትልቅ ሥፍራ የሚሰጣቸው በአሜሪካኖች ትውስታ ብቻ አይደለም። እያንዳንዱ የለማ ሀገር እንደዚህ ዓይነት ጀግኖች አሉት። ሁላችሁም ታውቋችሁዋላችሁ ብዬ የምገምተውን የኮሪያን ኮንግሎመሬቶች ("ቻድቦል" ይሏቸዋል ኮሪያኖች) እንድጠቅስ ፍቃዳችሁን እጠይቃለሁ። በተለይ ሁለቱ በኛ አገር ሳይቀር "የጓዳ ስሞች" እየሆኑ ነው። እነዚህም ሳምሰንግና ሂዩንዴይ ናቸው። ኮሪያን ከለሚ አገር ወደለማች አገር ያሸጋገርዋት እነዚህ ሁለቱና በጣት የሚቆጠሩ ሌሎች ቻድቦሎች ናቸው ተብሎ በሰፊው ይታመናል። በኮሪያ ሕዝብ አእምሮ ውስጥ ቀርቶ በዓለም ዙሪያ ባሉ የልማት ኤኮኖሚስቶች ረገድም ዛሬ ታላቅ ሥፍራ ይሰጣቸዋል።

አሁን እዚህ የአሜሪካንን "የኢንዱስትሪ አምበሎች" ሆነ የኮሪያን ቻድቦሎች የማነሳው ከኛ አገር ጋር ለማነጻጸር አይደለም። ይቅርና አሜሪካ፤ የኮርያም ሁኔታ ከእኛ ጋር ተመሳሳይ አልነበረም።

እነሳምሰንግና ሂዮንዳይ የተነሱባት የ1950ዎቹ ኮሪያ ከዛ በፊት ከ100 ዓመት በላይ በልማት ኅዳና የተጓዘች፣ ሊሚላ የተቃረበ መሠረተ ልማትና የትምህርት አቅርቦት የነበራት፣ የገንዘብ ተቋሞች ደረጃና የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የሰፋና ከተሜው ከገጠሬው የላቀበት፣ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰች ነበረች። እነቀኛዝማች ተካ ኤገኖ መነሳት የጀመሩባት የ1950ዎቹ ኢትዮጵያ ግን ገና ለልማት በሯን የከፈተች አገር ነበረች። ስለዚህ እነቀኛዝማች ተካ ፈር ቀዳጅ አንትርኘረነሮች ነበሩ ማለት ይቻላል።

የአሜሪካንን ሆነ የኮሪያን ምሳሌ እዚህ የማነሳው በዚህ በፈር ቀዳጅነታቸው ቀኛዝማች ተካም ሆኑ ሌሎቹ በጊዜው የነበሩ ባልደረቦቻቸው ሊታወቁና በሀገራችን ህዝብ ትውስታ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ሊሰጣቸው ይገባል ለማለት ነው። ቀኛዝማች ተካ ከዛ ዘመንም አልፈው፣ የደርግን ጊዜ ተሻግረው ዛሬም አንትርፕረነር ናቸው። በዚህም ልናውቃቸውና ልናደንቃቸው ይገባል። ባጭሩ ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ጀግኖች ያሏት መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል።

ስለዚህ ይህ ውይይት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊኖር የሚገባውን የዕውቀት ማስተላለፍ ቀጣይነት ለማጠናከር ይረዳል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

የዛሬው ኘሮግራም ከወትሮው በተለየ በቀኛዝማችና በእንግዶቻችን መካከል በሚደረግ ውይይት ይከናወናል። ለዚህ መግቢያ እንዲሆነን ግን የሕይወት ታሪካቸው ዋና ዋና ምዕራፎች በጽሑፍ ይቀርብልናል።

ይህን ጽሑፍ የሚያቀርብልን ለአያሌ አመታት የቀኛዝማችን ሕይወት ታሪክ ሲከታተል የቆየው አቶ መኰንን ተገኝ ነው። አቶ መኰንን የመጀመሪያ ዲግሪውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታሪክ ያገኘ ሲሆን፣ የመመረቂያ ጽሑፉም በጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ሕይወት ላይ ነበር ያተኮረው። ጥናቱን ወደ ቢዝነስ ታሪክ መስክ በመቀየር፣ በዚሁ የታሪክ ክፍለ ትምህርት የማስትሬት ድርሳኑን በቀኛዝማች ተካ ኤገኖና በቀኛዝማች ሞላ ማሩ ላይ አቅርቧል። ዛሬ የሚያካፍለን የዚህን ጥናት እፍታ ነው።

የምሽቱን ኘሮግራም ፐ/ር ባሕሩ ዘውዴ የማጥመ ሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተር አጭር የመክፈቻ ንግግር በማድረግ ይከፍቱልናል፤ አመሰግናለሁ።

ሽፈራው በቀለ
የፕሮግራሙ አስተባባሪ

# የመክፈቻ ንግግር

**የተከበራችሁ እንግዶች!**

***በመጀመርያ «ከድኅነት ወደ ልማት:- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ» በተሰኘው የሁለተኛ ዙር መክፈቻ ፕሮግራም ለመገኘት እንኳን ደኅና መጣችሁ በማለት በማኅበራዊ ጥናት መድረክና በራሴ ስም ልባዊ ስሜቴን እገልፃለሁ::***

***የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ከተቋቋመ ከ1990 ዓ/ም ጀምሮ ፖሊሲ ነክ ምርምር በማካሄድና በዚህም ላይ ተመሥርቶ በልማት ጉዳዮች ላይ የሰከነ ውይይት በማስተናገድ ኢትዮጵያ አገራችን የልማትና የመልካም አስተዳደርን ጎዳና እንድትይዝ የበኩሉን አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቷል:: ይህንንም ዓላማ መሠረት በማድረግ እስካሁን ድረስ በገጠር ልማት፣ በመረጃ አቅርቦት፣ በትምህርት፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በምግብ ዋስትና፣ በዴሞክራሲያዊ አስተዳደርና በሠፈራ ፕሮግራም ላይ ዐውደ ጥናቶች አካሂዷል:: ከዚህም በተጨማሪ በሥነ ፆታና አካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች አመለካከታቸውን ያንጸባረቁበት የምሽት ውይይቶች አዘጋጅቷል:: በተለይም የድኅነት ቅነሳ ስትራቴጂ በሚረቀቅበት ወቅት የሲቪሉን ማኅበረሰብ በማስተባበር በመጨረሻው ሰነድ ላይ የዚያ ማኅበረሰብ አስተዳደር እንዲንፀባረቅ ግንባር ቀደም ሚና ወስዷል::***

***የነዚህ ዐውደ ጥናቶችና ውይይቶች ውጤቶችም ታትመው በመሰራጨታቸው የሕዝቡን፣ የፖሊሲ አውጭዎችንና አስፈፃሚዎችን ግንዛቤ ለማዳበር ረድተዋል ብለን እንገምታለን:: እነዚህ የሕትመት ውጤቶችና ሌሎችም ፖሊሲ ነክ መጻሕፍትና መጽሔቶች በአገር ውስጥና ካገር ውጭም የተሰራጨ ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመጣው የድርጅቱ መጻሕፍት ቤትም ለተመራማሪዎች ጠቃሚ ከሆኑ ሌሎች መረጃዎች ጋር ይገኛሉ::***

***ይሁን እንጂ፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ዋና ባለቤት ከሁሉም በላይ ሕዝቡ መሆኑ ስለታመነበት፣ ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ ማጥመ በኤፍ. ኤም አዲስ «ደወል» የተሰኘ የሬድዮ ፕሮግራም በሳምንት ሶስቴ ሲያስተላልፍ ቆይቷል:: የዚህን ፕሮግራም አበረታች ውጤት በማጤንም፣ ካለፈው ጥር ጀምሮ በደቡብ ሬድዮ «ጀምበር» የተሰኘ ሌላ ፕሮግራም በየሳምንቱ እሑድ ጠዋት ማስተላለፍ ጀምሯል::***

***የማጥመ መሥራች አባላት የድርጅቱን የምርምር መርሀ ግብር በሚነድፉበት ወቅት አንዱ ያተኮሩበት ጉዳይ ዕውቀትን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ ነበር:: ሆኖም በድርጅቱ የመጀመርያ ምዕራፍ የተለያዩ አጣዳፊ ሥራዎች ከፊቱ በመደቀኑ፣ በዚህ ርዕስ ላይ የጎላ እንቅስቃሴ ሳይደረግ ቆይቶ ነበር:: ድርጅቱ በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ተልእኮውንና ፕሮግራሙን በስፋት በመረመረበት ወቅት ግን ርዕሱ ልዩ ትኩረት እንደሚያስፈልገው በመረዳት፣ በሚቀጥለው ዓመት «ከድኅነት ወደ ልማት፣ እውቀትን ለትውልድ ማስተላላፍ» የተባለውን ፕሮግራም***

*ቀርፆ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡ እስከ ሚያዝያ 1998 ድረስም፣ ስምንት ተናጋሪዎች በተለያዩ ርእሶች ላይ በመናገር ሰፊ ልምዳቸውንና እውቀታቸውን ለተከታይ ትውልድ ማስተላለፍ ችለዋል፡፡*

*የዚህ ፕሮግራም ዓይነተኛ ዓላማ፣ ባለፉት ዐሥርት ዓመታት በኢትዮጵያ ሕይወት ውስጥ እየታጣ የመጣውን የፖሊሲ ቀጣይነትና ተከታታይነት ችግር በመጠኑም ቢሆን ለመፍታት ነው፡፡ ተከታታይ ትውልዶችን የሚያገናኝ ድልድይ በመዘርጋት፣ ያገር ልማት ይበልጥ የሚሠምርበትን መንገድ ለመቀየስ ነው፡፡ ማናቸውም ትውልድ የእውቀት ሞኖፖል አለው ብለን አናምንም፡፡ መጪው ትውልድ ያለፈውን ተግባርና ተሞክሮ መርምሮ፣ ድክመቱን አስወግዶ፣ ጠንካራ ጎኑን አጎልብቶ በዚያ ላይ ሲገነባ ብቻ ነው ብሔራዊ እድገት ሊገኝ የሚችለው፡፡*

*ከዚህ እምነት በመነሳትና፣ ያለፈውን ዙር አመርቂ ውጤት በመገንዘብም ነው ማጥመ ይህን ፕሮግራም ለሁለተኛ ዙር እንዲቀጥል የወሰነው፡፡ በተሠራጨው የኘሮግራም ማስተዋወቂያ ጽሑፍ (ብሮሹር) ላይ እንደተመለከተውም፣ በዚህኛው ዙር 11 አንጋፋ ኢትዮጵያውያን ልምዳቸውንና እውቀታቸውን ሊያካፍሉን ፕሮግራም ተይዞላቸዋል፡፡*



*ይህን ሁለተኛውን ዙር እንዲከፍቱልን የተመረጡት የዛሬው እንግዳችን ቀኛዝማች ተካ ኤገኖ ናቸው፡፡ ስለቀኛዝማች ተካ ማንነት ከዚህ መግቢያ ንግግር በኋላ በዝርዝር የሚቀርብ በመሆኑ፣ ጊዜ መሻማት አልፈልግም፡፡ መጥቀስ የምፈልገው፣ በቅድመ-አብዮት ኢትዮጵያ ውስጥ ከምንም ተነስተው ከፍተኛ ንብረትና ዝና ለማፍራት ከበቁት ኢትዮጵያውያን መካከል ቀንጮ ሊባሉ የሚችሉ እንተርፕረነር መሆናቸውን ነው፡፡ በተለይም በነፃነት ማግስት የንግዱን ክፍለ ኤኮኖሚ*

ከባዕዳን እጅ ፈልቅቆ ለማውጣት በተደረገው የኢትዮጵያን ነጋዴዎችና ኢንቬስተሮች ትግል ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱ ናቸው:: በዚህም ጥረታቸው በዘመኑ ከፍተኛ ግምት የነበረው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት ተሸላሚ ለመሆን በቅተዋል::

እንዲህ እንዳሁኑ በጥቂት ዓመታት (አንዳንዴም በወራት) ከበርቴ መሆን በማይቻልበት ዘመን፣ እንደ እነ ቀኛዝማች ተካ ከሱቅ በደረቴነት ወይም ከጫማ ጠራጊነት ወደ ታላቅ ኢንቬስተርነት የተሸጋገሩ ታታሪዎች ገድል በኢትዮጵያ የግል ክፍለ ኤኮኖሚ ቢዝነስ ታሪክ ውስጥ ምን ጊዜም ልዩ ሥፍራ ይዞ ይኖራል::

በመጨረሻም በዚህ አጋጣሚ፣ እንዲህ ዓይነቱን ፕሮግራም ለማካሄድና ባጠቃላይም በተለያዩ ዘርፎች ለምናደርገው እንቅስቃሴ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉልንን ቋሚ አጋሮቻችንን፣ የኖርዌይ ኤምባሲ፣ የኔዘርላንድ ኤምባሲ፣ የአየርላንድ ኤምባሲና የእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦን ከልብ እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ:: እስካሁን ድረስ እንደ ማጥመ ያሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሳገር ይበጃል ያሉትን መርሀ ግብር በሥራ ለመተርጎም የቻሉት በአብዛኛው እንዲህ ካሉ የውጭ አገር አጋሮች በሚያገኙት ድጋፍ ነው:: በልማት እንደገፉት አገሮች ሁሉ በኢትዮጵያም የግሉ ክፍለ ኤኮኖሚ እንዲህ ያሉትን ለልማትና ለመልካም አስተዳደር የሚደረጉን አገር-በቀል ጥረቶች የሚያግዙበትና የሚያበረታቱበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ብለን ተስፋ እናደርጋለን:: የአድዋ መቶኛ ዓመት በተከበረበት ወቅት አገር ወዳድ ግለሰቦችና ድርጅቶች በዓሉ በድምቀት እንዲከበር ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ያደረጉትን ከፍተኛ ድጋፍ በግሌ በልዩ ስሜት የማስታውሰው ነው:: የነፃነት ተጋድሎን ለመዘከር የተደረገው ትብብር እንዲህ ያሉ ልማትና መልካም አስተዳደርን ለማበረታት የሚጥሩ ድርጅቶችን ድጋፍ በመስጠትም እንዲታይ ጥልቅ ምኞታችን ነው::

መልካም ቆይታ! ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ::

ባሕሩ ዘውዴ (ፕ/ር)
የማጥመ ሥራ አስፈጻሚ ዲሬክተር

# የቀኛዝማች ተካ ኤገኖ አጭር የሕይወት ታሪክ

**(ከ1919 ዓ/ም ...)**

**በመኮንን ተገኝ**

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በዛሬው ቀን የማህበራዊ ጥናት መድረክ «ከድህነት ወደ ልማት:- እውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ» በሚለው ወቅታዊና አርቆ ያስተዋለ ፕሮግራም ላይ ተሳታፊ በመሆን በህይወት ዘመናቸው ያካበቱትን የንግድ ልምዳቸውንና ስኬታቸውን እንዲያካፍሉን የጋበዘው ጎምቱውን ኢትዮጵያዊ ቀኛዝማች ተካ ኤገኖን ነው:: እንደምትመለከቱት ቀኛዝማች ተካ በአሁኑ ጊዜ ሰማንያኛ ዓመታቸውን የደፈኑ አረጋዊ ናቸው:: አሁንም እንደ ትናንቱ ሁሉ ስራ በመስራት የሚያገኙትን እርካታ ላለማጣት ደፋ ቀና ሲሉ የሚውሉና የንግድ ድርጅቶቻቸውን በማስፋፋትና ሌሎች አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በመንደፍና ወደ ስራ በመተርጎም ላይ ያሉ ታታሪና ስኬታማ ነጋዴ ናቸው:: ባጭሩ ለቀኛዝማች ህይወት ማለት መስራት መስራት አሁንም መስራት ነው:: ብዙ በመስራት በጣም ብዙ ስራ መፍጠር ነው::




ቀኛዝማች ስለራሳቸው ሲናገሩ እንደሚሉት «ከድህነት ዩኒቨርሲቲ የተመረቁ» ባለፀጋ ብቻ አይደሉም :: ቢያንስ:-

1ኛ. በወቅቱ ኋላቀር አመለካከት የነበራቸው ሰዎች ነጋዴንና የእጅ ባለሙያውን አናንቀውና አሳንሰው በሚያዩበት ወቅት ንግድን አቀላጥፎና በልጦ በመስራት አስተሳሰባቸው የተሳሳተ መሆኑን ካስመሰከሩት ወጣት ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች አንዱ ናቸው::

2ኛ. ከጥቃቅን የንግድ ዘርፍ በስተቀር መላው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በውጭ የንግድ ሰዎች ቁጥጥር ስር በነበረበት ወቅት ከዝቅተኛ ደረጃ በመነሳት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ እመርታ በማድረግ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በመንግስት ድጋፍ ሳይሆን በግል ጥረታቸው ነፃ ለማውጣት ተቃርቦ የነበረው ወጣት የንግድ ማኅበረሰብ ቁንጮ አባል ናቸው::

እስከ አድዋ ድል ድረስ የነበረው አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ ደግሞ የደጋው ክርስቲያን ከግብርና በስተቀር የጉልበት ሥራን እና ንግድን አሳንሶና አናንቆ የሚመለከት ነበር:: በዚህም የተነሳ የንግዱን ዘርፍ የተቆጣጠሩት የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ኢትዮያውያንና የውጭ አገር ነጋዴዎች ነበሩ:: ነጋዴዎችና የእጅ ስራ ባለሙያዎች ለህዝቡም ሆነ ለቤተመንግስት ሰዎች ከፍተኛ አገልግሎት ቢያበረክቱም ከህብረተሰቡ የተገለሉ በአብዛኛው ጊዜ ለጋብቻ የማይመጥኑ በውትድርና ዓለም በመግባት አገራቸውን ለማገልገል የማይፈቀድላቸውና በተለይ የእጅ ሞያ አዋቂዎች የመሬት ባለቤትነት የተነፈጋቸው ነበሩ:: ከአድዋ ድል በኋላ አንደኛ አገሪቱ ከውጪው ዓለም ጋር ቀጥተኛና ዘላቂ የሆነ ግንኙነት ስትመሰርት ኋላቀር አመለካከቱ ቀስ በቀስ እየተፈረካከሰ መምጣት ጀመረ:: በተለይ ደግሞ የአዲስ አበባ - ጅቡቲ ምድር ባቡር ስራ ሲጀምር ከውጭ ወደ አገር ቤት የንግድ ዕቃዎችን በገፍ እንዲገቡ ያስቻለ ብቻ ሳይሆን እግረ መንገዱን የካፒታሊስት ባሕል እና እሴቶች አብረው ወደ ኢትዮጵያ እንዲዘልቁ ያደረገ ነበር:: በዚህ የተነሳም የቤተመንግስት ሰዎች ከተራው ኢትዮጵያዊ ቀድመው በንግድ ዓለሙ ውስጥ ተሰማሩ:: የሚገርመው ደግሞ በዘመናዊው ንግድ ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ የመጀመርያው የሆኑት ዳግማዊ ምኒልክ እና እቴጌ ጣይቱ ነበሩ:: በመቀጠል ታላላቅ መሳፍንቶቻቸው ተከተሉ::

በወቅቱ ሕዝቡ ለነጋዴዎችና ለእጅ ስራ ባለሞያዎች ያሳይ የነበረው ንቀትና አሳንሶ የማየት ልክፍት ዳግማዊ ምኒልክ ለጀመሩት ኢትዮጵያን ዘመናዊ የማድረግ ፖሊሲ አቸውን እንደሚያደናቅፍ ሲረዱ የሚከተለውን አዋጅ አወጡ::

*ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ*
*ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገስት ዘኢትዮጵያ*
*ሠራተኛን በሥራው የምትሰድብ ተወኝ*

*ከዚህ ቀድሞ ብረት ቢሠራ ጠይብ ሽማ ቢሠራ ሸማኔ ቢጽፍ ጠንቋይ ቤተክርስትያን ቢያገለግል ደብተራ እያላችሁ አርሶ ነጭ ከጥቁር አምርቶ የሚያገባውን አራሽ ከዘውድ ይበልጣል የሚባለውን ገበሬ እያላችሁ ነጋዴን ነገዶ ወርቁን ግምጃውን ይዞ ቢገባ አንተ ነጋዴ ገጣባ አጣቢ እያላችሁ ሰነፍ ብልጉን እየተሳደበ አስቸገረ:: ቀድሞም ይህ ሁሉ ፍጥረት የተገኘው*

ካዳምና ከሔዋን ነው እንጂ ሌላ ሁለተኛ ፍጥረት የለም ይህ ሁሉ ካለመማር የተነሣ ነው አዳምንም « ብላዕ በሀፈ ገጽከ » ብሎታል ይህ ከቀረ ሁሉ ቦዘንተኛ ከሆነ መንግስት የለ አገር የለ በወዲያ አገር ግን ባውሮፓ ሁሉ አዲስ ሥራ አውጥቶ መድፍ ነፍጥ ባቡር ቢሠራ መሐንዲስ እየተባለ እየተመሰገነ ሠራተኛውም ብዙ ይጨመርበታል እንጂ በሥራው አይሰደብበትም እናንተ ግን እንዲህ እየተሳደባችሁ ማረሻ የሚያሾል አሳጥታችሁ አገሬን ባዶ ልታደርጉትና ልታጠፉት ነው፡፡

እንግዲህ ግን እንዲህ ብሎ የተሳደበ እኔን የሰደበ ነው፡፡ እንጂ ሌላውን መስደብ አይዶለም ዳግመኛ ግን ሲሳደብ የተገኘ ሰው መቀጫውን አንዳንድ ዓመት ይታሠራል ሹማሞችም አስረኽ ዓመት ለማስቀመጥ የሚቸግርኽ የሆነ እንደሆነ አስረክ ወዲህ ስደድልኝ፡፡

ጥር ፲፯ ቀን ፲፱፻

ዓዋጁ እንዳሳየን ነጋዴና የእጅ ስራ ባለሞያዎች ባብዛኛው ሰው ይታዩ የነበረው እንደ «ሁለተኛ ፍጥረት» ነበር፡፡ ነገሩን ለማሳጠር አንዲት ሴት ነገሩ ጭንቅ ቢላት ያለችውን ብንጠቅስ እንወዳለን፡፡ ሴትዮዋ የጋብቻ ጥያቄ ይቀርብላታል፡፡ ሆኖም ጥያቄውን ያቀረበው ሰው የማይመጥናት መስሎ ቢታያት

አወይ ጉዴ
ላግባሽ አለኝ ነጋዴ

አለች ይባላል፡፡ እንግዲህ እነ ቀኛዝማች ይህን ሁሉ ታግለው ስላሸነፉ ነው ያሁኑ ነጋዴ ጋብቻን ለመሰለ ታላቅ ጉዳይ የሚፈለግ ብቻ ሳይሆን ሰው ሁሉ ወዳጄ ጓደኛዬ ነው ብሎ ለመመካት የሚጥረው፤

## ቀኛዝማች ተካ ማን ናቸው?

ቀኛዝማች ተካ ኤገኖ በ1919 ዓ/ም ቡታጅራ አጠገብ በምትገኘው ኢሌ ተብላ በምትጠራ መንደር ተወለዱ፡፡ አባታቸው አቶ ኤገኖ ሸመቶ የመስቃን ጉራጌ ተወላጅ ሲሆኑ እናታቸው ወይዘሮ ደልጩሜ አሴገዮ ደግሞ የክስታኔ ጉራጌ ናቸው፡፡ እናታቸው ኢሌ ውስጥ በአነስተኛ ንግድ ውስጥ ተሰማርተው ነበር፡፡ ቀኛዝማች ስለእናታቸው የንግድ ተሳትፎ ከእናታቸው የሰሙትን ታሪክ በፍቅር ነው የሚያስታውሱት፡፡ ስለሁኔታው ሲናገሩ «እናቴ የዘጠኝ ወር ነብሰጡር ሆና ሌላ ጊዜ እንደምታደርገው ሁሉ ጠዋት ተነስታ ለንግድ ያዘጋጀችውን ቁሳቁስ ተሸክማ ገበያ ወረደች፡፡ ቀኑን ሙሉ ስትነግድ ውላ ዘጠኝ ጠገራ ብር አትርፋ ወደ ቤት ተመለሰች፡፡ ምሽት ላይ ወንድ ልጅ ተገላገለች ያን ልጅ ደግሞ ተካ ብላ ሰየመችው፡፡»

ያለ መታደል ሆኖ ቀኛዝማች ገና የሰባት ዓመት ልጅ እያሉ አባታቸውን በሞት ተነጠቁ፡፡ የአቶ ኤገኖ ሞት ለቤተሰቡ መበታተን ምክንያት ሆነ፡፡ እናታቸው ሌላ ባል ማግባታቸው ነው ነገሩን ሁሉ የበለጠ ያበላሸው፡፡ እልኸኛውና በሌላ ሰው ቁጥጥር ስር መዋልን የማይወዱት ተካ ከናታቸው ጋር በመኖር በእንጀራ አባት ከመንገላታት በእድሜ ከኮሰሱት በኢኮኖሚ ከደቀቁት አያታቸው ጋር ለመኖር ቀያቸውን ጥለው ተሰደዱ፡፡

አያታቸው ቤት መኖር ጀምረው ብዙም ሳይቆዩ ሌላ ችግር ተፈጠረ፡፡ አባታቸው ሲሞቱ በውርስ የተገኘውን ሁሉ እንዲያስተዳድር

አደራ የተሰጠው የታላቃቸው ታላቅ የሆነው ወንድማቸው በአጉል ሱስ ተጠመደ:: ስራው በየቀኑ መረን የለቀቀ አልኮል መጠጣት ሆነ :: ውሎውም አዳሩም ከኮማሪቶች ጋር ሆነ:: የመጠጥ ሱሱን ለማርካትና ኮማሪት ጓደኞቹን ለማስደሰት ሲል ንብረቱን መሸጥ ጀመረ:: በመጨረሻ የእርሻ በሬዎችን ሲሸጥ በቤት ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ ጠፋ:: አባታቸውን በሞት እናታቸውን በእንጀራ አባት የአባታቸውን ንብረት በወንድማቸው የተነጠቁት ተካ መግቢያ መውጪያው ጠበባቸው:: በዚህ ጊዜ የመጣው ይምጣ በማለት ወደ አዲስ አበባ ለመሰደድ ቆረጡ::

ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ሲጀምሩ መንገድ ላይ ከዚህ በፊት የሚያውቁት ሰው ይገጥማቸውና ሰውየው ከሱ ጋር ትንሽ ቆይተው እንዲሄዱ ይጋብዛቸዋል:: ቀኛዝማችም ግብዣውን ተቀብለው ወደ ሰውየው ቤት አብረው ይሄዳሉ:: ይህ አጋጣሚ የዕድሜ ልክ ትምህርት ያገኙበት ሆነ:: በእንግድነት ባረፉበት መንደር ተስቦ ገብቶ ኖሮ ቀኛዝማች በበሽታው ተለከፉ:: ወዲያው ሌሎች በበሽታው የተያዙ ሰዎች ገለል ወደ ሚደረጉበት አንድ ቤተክርስትያን ተወሰዱ:: የወቅቱን አስከፊ ገጠመኝ እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል:: « በዛን ጊዜ ገና የ13 ዓመት ልጅ ስለነበርኩኝ በስፍራው በዕድሜ ትንሹና ይባስ ብሎ ደግሞ ዞር ብሎ የሚያይ የሚያስታምምና የሚያፅናና ዘመድ የሌለው ፍጡር እኔ ብቻ ነበርኩኝ:: ከዚህ በተጨማሪ ከሌላው ሰው ሁሉ በሽታው እኔን ክፉኛ ስለጎዳኝ አብረውኝ የነበሩ በሽተኞች ሁሉ በኔ ተስፋ ቆረጡ:: በሽተኛ በሞተ ቁጥር ሌሎች ከፍተኛ ዋይታ ያሰሙ ስለነበር የመንደሩ ሰው ሮጦ መጥቶ በመጀመርያ ይል የነበረው ውይ ያ ምስኪን ልጅ አረፈ ነበር:: ያኔ በጣም የሰቀጠጠኝ ጉዳይ ያን ያህል ብቸኛ መሆኔ ሲሆን ግርምት ያሳደረብኝ ደግሞ ለካስ ሞት ይህን ያህል ቅርብ ነው የሚል ሃሳብ ነበር:: ከወረርሽኙ የተማርኩትና በኋላ ላይ በንግድ ህይወቴ እንደ ትልቅ ትምህርት የሆነኝ እንኳን ሌላ ሌላው ይቅርና ተስፋ ሳይቆርጡ በርትተው ከጣሩ ሞትንም ማሸነፍ እንደሚቻል ነው::»

ከወረርሽኙ እንደተረፉ በቀጥታ ጉዟቸውን ወደ አዲስ አበባ አቀኑ:: ቀኛዝማች ወደ አዲስ አበባ በሚጓዙበት ጊዜ ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ከጣልያን ቁጥጥር ስር ነፃ የወጣች ብትሆንም አንዳንድ ሰዎች ዋናውን መንገድ ተከትለው በተጓዥ ላይ የስርቆትና የውንብድና ተግባር ይፈፅሙ ስለነበር ዋናውን መንገድ በመተው ተራራዎችን በማሳበር በአጨበር በኩል በማቋረጥ ነው ዋና ከተማው የደረሱት::

አዲስ አበባ ውስጥ ታላቅ ወንድማቸው የሆነው ደበላ ኤገኖ በልብስ ስፌት ሞያ ላይ የተሰማራ ስለነበር በቀጥታ መርካቶ በመሄድ አገኙት:: ይህም የሆነው የልብስ ስፌት ሙያን በብዛት ይሰሩ የነበሩት ጉራጌዎች ስለነበሩ አንዱ የሌላውን አድራሻ ያውቅ ስለነበር ነው:: ከወንድማቸው ጋር በተገናኙ ትንሽ ሰዓታት ውስጥ የአገር ቤት የልብ ወዳጃቸውን አርጋውን እዛው መርካቶ ውስጥ አገኙት:: ምንም እንኳን ታላቅ ወንድማቸው ቀደም ሲል ስለንግድ ጥቅምና እሳቸውም ነጋዴ ቢሆኑ እንደሚሻላቸው የመከራቸው ቢሆንም እኩያቸው የሆነው አርጋው ስኬቱን አንደምሳሌ አድርጎ ሲያጫውታቸው በሃሳቡ ይበልጥ ተማረኩ::

አርጋው ስለ ንግድ ጥቅም ሲያስረዳቸው «አሁን እኔ አምሳ ማርትሬዛ ያህል ገንዘብ ያጠራቀምኩት ስለነገድኩኝ ነው፡፡ በል እንካ ይቺን አንድ ማርትሬዛ ተቀበልና በቀጥታ ወደ ንግዱ ተሰማራ» አላቸው፡፡ ቀኛዝማችን ያኔ ያስደመማቸው «በእውነት አሁን እኔ እድሜዬን በሙሉ ብነግድ እንደ አርጋው አምሳ ማርትሬዛ አገኝ ይሆን?» የሚለው ሃሳብ ነው፡፡

ደበላ የሰጣቸውን አንድ ማርትሬዛ አርጋው ከሰጣቸው አንድ ማርትሬዛ ጋር በመጨመር በነጋታው በጥዋቱ ዳቦ በመግዛት በየመንገዱ መሸጥ ጀመሩ፡፡ ገጠሬነታቸውን የተመለከቱ ልጆች አንድም የያዙት ዳቦ ጥራት የሌለው መሆኑን እያበሉ በርካሽ ለመግዛት ሲጥሩ ሲመች ደግሞ ገንዘባቸውን ለመንጠቅ ቢጣጣሩም እንደምንም ብለው የያዙትን ዳቦ ሸጠው ቤት ገቡ፡፡ ታዲያ ምን ያደርጋል በነጋታው ከተማ ውስጥ ሲዘዋወሩ ሰዎች እጅብ ብለው ቁማር ሲጫወቱ ሲመለከቱ እስቲ እኔም እድሌን ልሞክር ብለው ገብተው በቁማር ስለተበሉ ያላቸውን ገንዘብ ሁሉ አስረክበው እጃቸውን አጨብጭበው ተመለሱ፡፡ በነጋታው እስከዛሬ ድረስ ሲያስታውሱት የሚያንገበግባቸውን ስራ ፈፀሙ፡፡ በህይወታቸው ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ የሌላ ሰው የደሞዝ ተቀጣሪ ሁነው ዋሉ፡፡ አንድ ጋዝ መሸጫ ቤት በጋዝ አከፋፋይነት በቀን አንድ ማርትሬዛ ተቆርጦላቸው ተቀጠሩ፡፡ አመሻሹ ላይ አንድ ማርትሬዛውን ዕንባ እየተናነቃቸው ተቀብለው ሁለተኛ ተቀጣሪ ሰራተኛ ላለመሆን ምለው ተገዝተው ወደቤት ተመለሱ፡፡

በዛች አንድ ማርትሬዛ መርካቶ አሁን አዳራሽ በተሰራበት አካባቢ ከሚገኝ የአንድ ኢጣልያዊ ሸንኮራ ማከፋፈያ መጋዘን ሸንኮራ አገዳ በመግዛት ሌላ ሰፈር ይዘው በመሄድ በትንሽ በትንሹ እየቆራረጡ መቸርቸር ጀመሩ፡፡ ገበያው ደራላቸውና እየተመላለሱ ከመጋዘኑ ሸንኮራ አገዳ እየገዙ ሲቸረችሩ አርፍደው በረፋዱ ገበያ ብቻ ከ3 ማርትሬዛ በላይ አተረፉ፡፡ በትርፉና በስኬቱ የተደሰቱት ተካ ባላቸው ገንዘብ በሙሉ ሸንኮራ ገዝተው ወደ ተለመደው ቦታ አቀኑ፡፡ ሁኔታውን አድፍጠው ይመለከቱ የነበሩ የከተማ ወሮበሎች እጅብ ብለው በመምጣት ለኔ ይህን ያህል ለኔ ደሞ ይህን ያህል በማለት ከከበቡአቸው በኋላ ሁሉም የቻለውን ያህል በመንጠቅ በተለያየ አቅጣጫ ሮጡ፡፡ በሁኔታው የተደናገጡት ተካ ሰውነታቸው ደነዘዘ፡፡ እንኳን ልጆቹን አሯሩጦ ለመያዝ መሞከር ይቅርና ዓይናቸውንም ማመን ቢያቅታቸው ፈዘው ቀሩ፡፡ ይሄኔ በተደጋጋሚ በደረሰባቸው ኪሳራ ተደናግጠው ተስፋ እንደመቁረጥ ቢሉም እንደገና ራሳቸውን ካረጋጉ በኋላ አሁንም የመጣው ይመጣል እንጂ መነገዴን አላቋርጥም በማለት ለራሳቸው ቃል ገቡ፡፡ ይህ በአፍላ እድሜያቸው ያጋጠማቸው ወድቆ የመነሳት ትግል ኋላ ላይ ያጋጠማቸውን እክልና እንቅፋት በፅናት እየተቋቋሙ በማለፍ ስኬታማ እንዲሆኑ ረድቷቸዋል፡፡

እዚህ ላይ ያሁኑን የቀኛዝማችን ህይወት በጥሞና ለማየትና በንግድ ስኬታቸው ላይ ትምህርት አስተዋፅኦ አድርጓል ወይስ አላደረገም ብለን ለማመዛዘን ስለትምህርታቸው ደረጃ ትንሽ መልከት ማድረጉ አስፈላጊ ይመስለናል፡፡ የቀኛዝማች ተካ የትምህርት ደረጃ ከቤተ ክህነት

ትምህርት የዘለለ አይደለም ለዛውም ቢሆን በቅጡ አልተማሩትም። ቀኛዝማች ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ አባታቸው ልጃቸውን በመያዝ እተካ ክርስትና አባት ቤት በመውሰድ ልጄን አስተምርልኝ በማለት ይሰጡዋቸዋል። የተካ የክርስትና አባት ደብተራ ሀይሉ በወቅቱ የጨቦና ጉራጌ አውራጃ ገዢ የነበሩት የራስ ልዑል ሰገድ ፀሐፊ ነበሩ። ደብተራ ሀይሉ የሁለት ወንድና አንድ ሴት ልጅ አባት ቢሆኑም በወቅቱ ስለ ሴት ልጅ መማር ጥቅም አያውቁ ስለነበር ለሁለቱ ወንድ ልጆቻቸውና የክርስትና ልጃቸው ለሆኑት ለተካ እቤታቸው ውስጥ ዓለቃ ይስሀቅ የሚባሉ አስተማሪ ቀጠሩላቸው። ዓለቃ ይስሃቅ ጠንቃቃና ጎበዝ አስተማሪ ቢሆኑም የሃብታምም ይሁን የደሃ ልጅ ተማሪ እስከሆነ ድረስ ትምህርቱ የሚገለጥለት እንደ ሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የቆሎ ተማሪ ሁሉ ቀለባቸውን ከመንደሩ ነዋሪ ለምነው እንዲያገኙ ቀጭን ትዕዛዝ አስተላለፉ። ለጉዳዩ አዲስ ያልሆኑት ደብተራ ሃይሉም በሃሳቡ ተስማሙ። ሦስቱም ልጆች እንደታዘዙት በልመና ያገኙትን እየተመገቡ ትምህርታቸውን ቀጠሉ። ከጊዜ በኋላም ከሁኔታው ጋር እየተላመዱ ሲመጡ ለምኖ መብላቱን እንደመደበኛ የተማሪ ህይወት ወሰዱት። ከዕለታት በአንዱ አቶ ኤገኖ ልጃቸውን ለማየት ደብተራ ሃይሉ ወደሚኖሩበት ከተማ ወረዱ። ኤገኖ ልጃቸው አቁማዳ ይዞ የሰው በር ላይ ቆሞ አገኙት። በነገሩ ግራ የተጋቡት አባት ምን እየሰራህ ነው ብለው ልጃቸውን ይጠይቃሉ። ልጅም በቤትክህነት ቀኖና ተማሪ ትምህርቱን እስኪጨርስ ድረስ ለምኖ መብላት አግባብ ስለሆነ ይህን እየፈፀምኩኝ ነው ይላሉ። አባት ግራ ይገባቸዋል። ቀኛዝማች ስለ ሁኔታው ሲያብራሩ «በጉራጌ ባህል ልመና በጣም የተጠላ ተግባር ስለሆነ አባቴ የምነግረውን ሁሉ አምኖ ለመቀበል አዳገተው። ይልቅዬ እኔን ከማድመጥ ልመና የሚለው ቃል ከመጠን በላይ ስላስቆጣው ንዴቱን ከኔ ለመደበቅ እስኪያቅተው ድረስ ፊቱ ልውጥውጥ አለ» ይላሉ። የልጃቸውን ማግባባት ወደ ጎን በመተው የልጃቸውን እጅ ጠፍረው በመያዝ ወደ ደብተራ ሃይሉ ቤት ገሰገሱ። እዛም እንደደረሱ «ደብተራ ሃይሉ ምነው ምን አጠፋሁ ምን በደልኩኝ ልጄን ዕውቀት አስተምርልኝ ብልህ ልመና ታስተምርብኝ» በማለት አምርረው ከተናገሩ በኋላ ልጃቸውን ይዘው ወደ መንደራቸው ተመለሱ። በዚች አጋጣም የቀኛዝማች የመማር ዕድል ተሰናከለ።

ወደ ወጣቱ ነጋዴ ተካ ኤገኖ የአዲስ አበባ እንቅስቃሴ ስንመለስ በኪሳራ ከተደመደመው የሸንኮራ አገዳ ችርቻሮ በመቀጠል በተለያዩ ጥቃቅን ንግዶች ላይ ከተሰማሩ በኋላ የተሸጋገሩት ወደ የገንዘብ ምንዛሬ ነው። ጣልያን ባልተመጣጠነ የጦር መሳሪያ ብልጫና በሕግ የተከለከለ የመርዝ ጭስ በመጠቀም በኢትዮጵያ አርበኞች ላይ ጊዜያዊ ድል በማግኘት የተወሰነውን የአገሪቱን ግዛት በተቆጣጠረበት አምስት ዓመታት ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ በምኒልክ ብርና በማርትሬዛ ይካሄድ የነበውን ግብይት በማስቆም ሊሬ በሚባለው የራሱ ገንዘብ እንዲተካ ማድረጉ ነው። በዚህ ወቅት ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ከጣሊያሊን ወታደሮች ባንዳዎችና ሴተኛ አዳሪዎች ሊሬ በመሰብሰብ

*በምኒልክ ብርና ማርትሬዛ ይመነዝሩት ነበር፡፡ ተካና እኩዮቻቸው ወደ ምንዛሬ ንግድ የተሰማሩት ግን ጣልያን ከኢትዮጵያ በሽንፈት ከተባረረች በኋላ ነበር፡፡*

*በዚህ የተነሳ እነ ቀኛዝማች በጥብቅ ይፈልጉ የነበረው የእንግሊዝ ጦር ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴን በማገዝ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ይዞት የመጣውን የኢስት አፍሪካ ሽልንግን ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ከጣልያን ወረራ ራሷን ነፃ ብታወጣም ከ1933 እስከ 1937 ዓ.ም በነበሩት ዓመታት ለእርዳታ የመጣው የእንግሊዝ ጦር የተለያዩ ተልካሻ ምክንያቶችን በመፍጠር አገሪቱን በተዘዋዋሪ የቅኝ አስተዳደር ስር ለማቆየት ያላሰለሰ ጥረት ያደርግ ስለነበር ኢትዮጵያ የኔ የራሴ ነው የምትለው የመገበያያ ገንዘብና የፋይናንስ ተቋም አልነበራትም፡፡ ይህም ስለሆነ የእንግሊዝ ጦርና ከቅኝ ግዛቶቹ ያመጣቸው ወታደሮች ብቻ ሳይሆኑ ኢትዮጵያን አርሚ ተብሎ ይጠራ የነበረው የአገሪቱ መከላከያ ጦር ሳይቀር ደሞዙን ያገኝ የነበረው በኢስት አፍሪካ ሽልንግ ነበር፡፡ የእንግሊዝን ጦር ጨምሮ ቅኝ ግዛቱ ከነበሩ ደቡብ አፍሪካ፣ ሕንድ፣ ግብፅ ሱዳንና ኬንያ ያመጣቸው ወታደሮች ያገር ውስጥ ምርቶችን በተለይ ደግሞ ለምግብ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን ከኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች መግዛት ሲፈልጉ አገሬው የሚጠቀምበትን ማርትሬዛ ማግኘት ግድ ስለሆነ በቀጥታ ያመሩ የነበረው ወደ ገንዘብ መንዛሪዎቹ ነበር፡፡*

*ተካና እሳቸውን መሰል ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በገንዘብ ምንዛሬ ንግድ ላይ ይሰማሩ እንጂ በቂ ገንዘብ ስላልነበራቸው ንግዱን ከበላይ በመሆን ይቆጣጠሩ የነበሩት ሕንዶች ነበሩ፡፡ ታዲያ ሕንዶቹ ለግብይቱ የሚሆነውን አነስተኛ ገንዘብ ይዞ ለሚመጣ ኢትዮጵያዊ ነጋዴ የያዘውን ገንዘብ በማርትሬዛ ለውጠው በመስጠት ሽልንጉን ማታ ይዞ መጥቶ እንዲያስረክባቸው ሲያደርጉ እንደ ቀኛዝማች ተካ ዓይነቱ ታማኝና ልምድ ያለው ንቁ ነው ለሚሉት ደግሞ አነስተኛ ገንዘብ ብድር በመስጠት እንዲነግድ ይረዱት ነበር፡፡ በተደጋጋሚ ኪሳራ ገንዘብ አልባ የሆኑት ተካ ይህን ዕድል በመጠቀም ነበር ወደ ምንዛሬው ንግድ የገቡት፡፡ የገንዘብ ምንዛሬው ይካሄድ የነበረው በከተማዋ የተለያዩ ቦታዎች ነበር፡፡ ንግዱ ይካሄድባቸው የነበሩት ዋና ዋናዎቹ ቦታዎች አዲስ አበባ እምብርት ላይ አሁን አራዳ ገበያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ፣ ሜክሲኮ አደባባይና እስከ አሁን ድረስ መርካቶ ውስጥ ምንዛሬ ተራ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ ነበር፡፡*

*በወቅቱ አንድ ኢስት አፍሪካ ሽልንግ በአፊሴል ይመነዘር የነበረው በአስር ማርትሬዛ ነበር፡፡ ነጋዴዎቹ ግን በአቅርቦትና ፍላጎት ላይ በመመስረት አንዱን ሽልንግ በሰባት ማርትሬዛ መመንዘር ጀመሩ፡፡ በሽልንግ ደመወዛቸውን ተቀብለው ለምንዛሬ የሚመጡት የኢትዮጵያን አርሚ ወታደሮች በሁኔታው በመቆጣት ድርጊቱን አይን እንዳወጣ ዝርፍያ ይቆጥሩታል፡፡ በዚህ የተነሳ መጀመሪያ ላይ በማስፈራራትና በንጥቅያ አንዱን ሽልንግ በአስር ማርትሬዛ ተመን መውሰድ ጀመሩ፤ ሆኖም ነጋዴዎቹ ራሳቸው ባወጡት ተመን ንግዱን ይቀጥላሉ፡፡ አሁን ወታደሩ እነሱ ባሉት ካልሆነ የግድያ ዛቻ መሰንዘር ይጀምራሉ፡፡ ከጥቂት*

ነጋዴዎች በስተቀር የተቀረው ፍንክች አልል አለ፡፡ የአብዛኛው ነጋዴ እምቢ ባይነትን እንደ ዐመፅ በመቁጠር ወታደሮቹ ጉዳዩን ለበላዮቻቸው ያሳውቃሉ፡፡ ጉዳዩ ንጉሥ ነገስቱ ድረስ ይሄዳል፡፡ በወቅቱ በተለያዩ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግሮች የተነሳ ጫና ስር የነበረው የኢትዮጵያ መንግስት ተጨማሪ ጠላት ከማፍራት በማለት ይመስላል ከጦሩ ጋር በመወገን በእምቢተኛ ነጋዴዎች ላይ የጅራፍ ቅጣት ይወስናል፡፡ በዚህ የተነሳም ሶስት ነጋዴዎች ተይዘው ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ በጅራፍ ሲቀጡ እነ ቀኛዝማች ጎመን በጤና ብለው ንግዱን እርግፍ አድርገው ይተውታል፡፡ ተመሳሳይ ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ እንደሚያደርጉት ሁሉ ፊታቸውን ወደ ሌላ የንግድ ዘርፍ ለማዞር ወደ ንግድ ጥናት ይገባሉ፡፡

አዲስ የንግድ ዓይነት ለማግኘት በማፈላለግ ላይ እያሉ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቀጥተኛ ትዕዛዝ በከተማዋ በቁጥር ብዙ የሆኑትን የውጭ አገር ዜጎች በተለይ ደግሞ አብላጫውን የያዙት ጣልያኖች የሚፈልጉትን ቁሳቁስና አገልግሎት የሚያቀርቡ በቂ ሱቆች ስላልነበሩ ወጣት ኢትዮጵያውያን ተመልምለው በተለያዮ የሱቅ በደረቴነትና በጫማ ጠራጊነት እንዲሰማሩ ተደረገ፡፡ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ከቀረቡት መስፈርቶች በወቅቱ የሁሉም የውጭ ዜጎች መግባቢያ (Lingua Franca) የሆነውን ጣልያንኛ ቋንቋ መናገር የሚችልና ከዚህ በፊት በንግድ ስራ በመሰማራት በቂ ልምድ ያለው መሆን አስፈላጊ ነበር፡፡ ጣልያንኛን በበቂ ሁኔታ መናገር የሚችሉትና በቂ ልምድ የነበራቸው ተካ ውድድሩን በማለፍ ሲጋራ በማዞር ንግድ ላይ እንዲሰማሩ ከተመረጡት ሰባ አምስት ወጣቶች አንዱ ሆኑ፡፡ የተለያየ የሱቅ በደረቴነት የመነገድ ዕድል ቀርቦ ለምን ሲጋራ ማዞሩን እንደመረጡ ሲናገሩ «ሲጋራ አዟሪነትን ከሌሎች አብልጬ የመረጥኩት በወቅቱ የበለጠ አትራፊ ንግድ እንደነበር አውቅ ስለነበር ነው» በማለት ያስረዳሉ፡፡ «በወቅቱ የመመረጥ ዕድሉን ያላገኙትም ሆነ በሌላ ሱቅ በደረቴነት ላይ የተሰማሩት ሁሉ የሲጋራ አዟሪነትን ትርፋማነት እየቆዩ ሲረዱት የንግድ ፈቃዳችንን እስከ ሁለት መቶ ማርትሬዛ ብር ለመግዛት ያግባቡን ነበር፡፡ ሆኖም ጣልያኖች ኢትዮጵያን ጥለው ሲሄዱ የሲጃራ ሱቅ በደረቴነት የማያዋጣ ሆነ፡፡ በዚህን ጊዜ ተካን ጨምሮ አብዛኛዎቹ ንግዱን ትተው ወጡ፡፡ እንደ ሁሌው አንድ ንግድ አላዋጣ ሲል እንደሚያደርጉት ለትንሽ ጊዜ ላይ ታች በማለት የንግዱን ሁኔታ እያጠኑ ቆዩ፡፡ በመሃል ወደ አገር ቤት በመሄድ የመጀመሪያ ባለቤታቸውን አገቡ፡፡ ባለቤታቸውን ገጠር በመተው ወደ አዲስ ሰበባ በመመለስ እንደገና ወደ ንግድ ዓለም ተመለሱ፡፡ ሆኖም የመጀመሪያው ትዳራቸው ዘላቂ መሆን አልችል ብሎ በፍቺ ተጠናቀቀ፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ የአልኮል መጠጥ ወደ አገሪቱ በማስገባት ከሕዝቡ ጋር ያስተዋወቁት ግሪኮች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ በተለይ ደግሞ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ በማስፋፋት ግሪኮች ቅድሚያውን ይይዛሉ፡፡ እነዚህ የግሪክ ነጋዴዎች የመጠጥ ንግዱ በአዲስ አበባ ብቻ ተወስኖ የተገደበ ሳይሆን በየጠቅላይ ግዛቱ በሚገኙ ከተሞች ሁሉ እንዲስፋፋ በነበራቸው ዓላማና በመሃላቸው በተፈጠረው

ከፍተኛ ፉክክር የተነሳ ወኪል የሚሆኑአቸው ኢትዮጵያውያንን ወደ መመልመሉ አመሩ:: ከጋብቻ መልስ ስራ ፈተው የነበሩት ተካ አንድ የመጠጥ ፋብሪካ ባለቤት የነበረ ግሪካዊ ወኪል እንዲሆኑት ጥያቄ አቀረበላቸው:: ቀኛዝማችን በወኪልነት እንዲያገለግሉት የፈለጋቸው ኮስታስ አንቶኒኖስ የተባለ የአነስተኛ መጠጥ ፋብሪካ ባለቤት የነበረ ሰው ነው:: አንቶኒኖስ ባለ ዶሮ የተባለ የመጠጥ ፋብሪካ ነበረው::

ባለ ዶሮ በአገሪቱ አንደኛ ደረጃን ይዞ ከነበረው በኒኮላስ ፓፓሲኖስ ይመረት ከነበረው ባለ ፈረስ መጠጥ ቀጥሎ ሁለተኛው ነበር:: ኒኮላስ ፓፓሲኖስ ማለት ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ታዋቂና ዝነኛ የመጠጥ ፋብሪካ ባለቤት ለመሆን የበቃውን ታናሽ ወንድሙን ማለትም ኤልያስ ፓፓሲኖስን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ በመምጣት እንዲሰራ የጋበዘ ሰው ነው:: ወደ ተካና አንቶኒኖስ ጉዳይ ስንመለስ ግሪኩ ወኪሎቹን ወደ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ወላይታ፣ ነቀምት፣ ጋሞጎፋ፣ አርሲና ወሎ ወደሚገኘው ካራቆሬ ሲልክ ቀኛዝማች ጅማ ሄደው እንዲነግዱ መደባቸው::

መጀመሪያ ላይ ተካ ጅማ በመመደባቸው ደስተኛ አልነበሩም:: እንደቀኛዝማች አመለካከት ምንም እንኳን ጅማን በአካል ተገኝተው ባያውቋትም በወሬ ይሰሙት እንደነበረው አብዛኛው የከተማው ነዋሪ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ስለሆነ ለአልኮል መጠጥ እጅግም ነው ባይ ነበሩ:: ሆኖም አንቶኒኖስ ስለጅማ ከተማና የመጠጥ ገበያው ከሳቸው የተሻለ የንግድ መረጃ ስለነበረው ቀኛዝማችን ያለመታከት በማግባባት ወደ ስፍራው እንዲሄዱ አደረገ:: በወቅቱ የመጠጥ ፋብሪካ ባለቤቶች በሆኑት ግሪኮች መሃከል በነበረው ከፍተኛ ፉክክር የተነሳ ወኪል የሚሆኑዋቸው ኢትዮጵያውያን በቂ ገንዘብ ሊኖራቸው እንደማይችሉ በመገንዘብ ታማኝና ቀልጣፋ ናቸው ላሉዋቸው መጠጡን በዱቤ ወስደው ከሸጡ በኋላ ገንዘቡን እንዲመልሱላቸው አመቺ ሁኔታ ፈጠሩላቸው::

ታህሳስ 19 ቀን 1942 ዓ/ም የ23 ዓመቱ ወጣት ቀኛዝማች ተካ ኤገኖ ከዚህ በፊት ከወሬ በስተቀር አይተዋት ወደማያውቋትና በሳቸውና በከተማዋ እንዲሁም ባካባቢዋ ባሉ ቦታዎችና ነዋሪዎቿ ሁሉ በታሪክ ሲወሳ የሚኖር ገድል ለመስራት ኮስታስ አንቶኒኖስ በዱቤ የሰጣቸውን ዘጠኝ መቶ ጠርሙስ ባለ ጆሮ የአልኮል መጠጥ አንዱን በአንድ ብር ሂሳብ የጣልያን ሲሪት በሆነ ያረጀ የጭነት መኪና ሸክፈው ከሾፌሩ ጎን በመቀመጥ ጉዞአቸውን ሀ በማለት ከአዲስ አበባ ተነሱ:: እንደዛሬው በዘመናዊ አቅድ ባልተሰራና በወላለቀው የጅማ አዲስ አበባ መንገድ ባሮጌው መኪና እየተናጡ በድካም ዝለው ከሦስት ቀን በኋላ እኩለ ሌሊት ገደማ ጅማ ደረሱ:: በነጋታው ጅማ ከደረሱ በኋላ ነገሮች ሁሉ ከጠበቁት በላይ የተገላቢጦሽ ሆኖ ጠበቃቸው:: የከተማው ህዝብ እንደጠበቁት የአልኮል መጠጥን እርም ያለ ሳይሆን ከገመቱት በላይ የሚጎነጨው መሆኑን በዓይናቸው በብረቱ ተመለከቱ:: ይባስ ብሎ ድንጋጤ ውስጥ የከተታቸው የተለያዩ የመጠጥ ምርቶችን በማከፋፈል የሚተዳደሩ የግሪክና የአርመን ነጋዴዎች ጅማ ውስጥ መከተማቸውን

ሲያውቁ ነው፡፡ ጅማ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ፉክክር በመፍራት ባቅራቢያው ወደ ሚገኝ ትንሽ ከተማ በመሄድ ያመጡትን መጠጥ መሸጥ እንዳለባቸው ወሰኑ፡፡

ከጅማ ጋር ስትወዳደር በጣም አነስተኛ ወደምትባለው አጋሮ ከተማ አፈገፈጉ፡፡ እዛም ቤት እሳት አለ እንደሚባለው ያልጠበቁዋቸው ሁለት ግሪኮች የከተማዋ መጠጥ አከፋፋዮች ሆነው ጠበቁአቸው፡፡ «ጉድ ነው አገሩ በሙሉ በውጭ ነጋዴዎች ተወሯል አይደል እንዴ» አሉ፡፡ ለጥቂት ጊዜ ጅማ በነበሩበት ወቅትና አሁን ደግሞ አጋሮ ውስጥ በታዘቡት ሁኔታ አገሬው ለነዚህ የውጭ ዜጎች ከፍተኛ ፍቅር ያለውና እምነትም የጣለባቸው ሆኖ ተሰማቸው፡፡ ተካ ያኔ ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ወጣ ገባውን ማጥናት ጀመሩ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ የመጀመሪያው ግምታቸው ስህተት መሆኑን ተገነዘቡ፡፡ አገሬው አማራጭ አጥቶ ነው እንጂ ከፈረንጆቹ ጋር የነበረው ትስስር ጥልቀት ያለው ሳይሆን ላይ ላዩን መሆኑን አረጋገጡ፡፡ በወቅቱ በአገሬውና በፈረንጅ ነጋዴዎች መሐል የነበረው ግንኙነት ምን ዓይነት እንደነበር ቀኛዝማች ባጭሩ እንዲህ ይገልጹታል፡፡

1ኛ. አጋሮ ከተማ በመጠጥ ንግዱ ላይ የተሰማሩት ሁለቱ ግሪኮች በሚያገኙት ትርፍ የረኩ ስለነበር በሌሎች ጨማሪ የንግድ ዘርፎች ላይ መሳተፍ ቀርቶ የያዙትንም ንግድ የማስፋፋት አዝማሚያ አልነበራቸውም፡፡

2ኛ. የግሪኮቹ የስራ ሰዓት እንደ ገበያው ሁኔታ የሚቀያየር ሳይሆን ዝንፍ የማይል ቋሚ ዓይነት ነው፡፡ ሱቆቹ ጠዋት በሶስት ሰዓት ተከፍተው ለምሳ በሰባት ሰዓት ላይ ይዘጋሉ፡፡ እንደገና በ9 ሰዓት ተከፍተው እስከ ምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ድረስ ግልጋሎት ይሰጣሉ፡፡ በሰንበትና በበዓላት ይከፈታሉ ማለት ዘበት ነው፡፡ ሱቆቹ በተዘጉበት ጊዜ ደንበኞች መጠጥ ፈልገው ወደ ግሪኮቹ ቤት ቢሄዱ የሚሰጣቸው መልስ ሱቁ ክፍት ሲሆን ተመለስ የሚል አጭርና ግልፅ መልስ ነበር፡፡

3ኛ. ፈረንጆቹ ራሳቸውን ልዩ ፍጡራን አርገው ይቆጥሩ ስለነበር በግብይት ወቅት በነጋዴውና በደንበኛው መካከል ከሚደረገው ግንኙነት ውጭ የዘለለ ግንኙት ከአገሬው ጋር አልነበራቸውም፡፡ ፈረንጆቹ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ከአገሬው ጋር ስላልፈጠሩ ራሳቸውን ያገለሉ ፍጡራን ነበሩ፡፡ አገሬው ጋር ተደባልቆ ከመተዋወቅ ይልቅ ትርፍ ጊዜያቸውን እርስ በርስ ካርታ በመጫወት ያባክኑ ነበር፡፡

ይህን ያስተዋሉት ተካ የመጀመሪያ እርምጃቸው ሱቃቸው ቀኑን ሙሉ ክፍት ማድረግ ብቻ ሳይሆን ደንበኛ እስከ መጣ ድረስ ምሽት ላይም ቢሆንም ለማስተናገድ ወሰኑ፡፡ በመቀጠል ከአገሬው ጋር መልካም ትስስር ማበጀት እንዳለባቸው በመገንዘብ ራሳቸውን ማስተዋወቅና ታዛዥ መሆናቸውን ማሳየት ጀመሩ፡፡ ምንም እንኳን አጋሮ ከተማ ትንሽ ብትሆንም አካባቢው የቡና አብቃይ አገር በመሆኑ አብዛኛው የከተማው ነዋሪም ይሁን ገበሬው በንፅፅር ከተቀሪው የአገሪቱ ክፍል ጋር ሲተያይ

የመግዛት አቅሙ ከፍተኛ ነበር:: ሆኖም ትንሿ አጋሮ ትቅርና ጅማ ራስዋ አገሬው የሚፈልገውን ዘመናዊ እቃዎች የማቅረብ አቅም አልነበራቸውም:: ይህን የተረዱት ተካ ያካባቢው ባላባቶችና ታዋቂ ሰዎችን ባገኙ ቁጥር አዲስ አበባ ለስራ ጉዳይ ስሄድ ምን ይገቬላችሁ ልምጣ በማለት ይጠይቁ ጀመር::

ያኔ አዲስ አበባ ካልሆነ በስተቀር በአካባቢዋ እንደልብ የማይገኙትና በነዋሪው ከፍተኛ ተፈላጊነት ከነበሩዋቸው ቁሳቁሶች መሃከል ከወርቅ የተሰሩ የጣትና የጆሮ ጌጣጌጦች፣ የተወሰኑ አልባሳት፣ ዘመናዊ ጫማዎች፣ ከቤት ዕቃዎች ለምሳሌ የሽቦ አልጋ፣ ባለቀለበቱ በርሜል እንዲሁም የድንጋይ ወፍጮና በዘመናዊ ወፍጮ የተፈጨ በርበሬ አንዳንዶች ነበሩ:: ነዋሪው እነዚህን ዕቃዎች ከአዲስ አበባ እንዲያመጡላቸው ቀኛዝማችን ሲጠይቁ ፈቃደኛ ቢሆኑም አንዳንድ እክሎች አላጡም:: ለምሳሌ አብዛኞዎቹ ነዋሪዎች ዘመናዊ ጫማ መጫማት ቢሹም ልካቸውን ወይም የእግራቸውን ቁጥር አያውቁም ነበር:: የሚመጥናቸውን ጫማ በትክክል ለማምጣት ሲሉ ቀኛዝማች የደንበኛቸውን እግር ካርቶን ወረቀት ላይ በማስቀመጥ በስክርቢቶ የእግሩን ቅርፅ ወረቀቱ ላይ ከነደፉ በኋላ ወረቀቱ ላይ ስም በመፃፍ አዲስ አበባ ድረስ ተሸክመው መሄድ ነበረባቸው:: ለጣት ቀለበት ፈላጊው ደግሞ የጣቱን ልክ ለማወቅ በጣቱ ዙሪያ ሽቦ በማሰር ከለኩ በኋላ ቋጠሮ በማበጀት መጠኑን ያውቁ ነበር::

ከዚህ በተጨማሪ የያኔዋ አጋሮ እንኳን ሆስፒታልና ክሊንክም ስላልነበራት እምነትዋን የጣለችው ሳሙኤል በሚባሉ የልምድ የጤና ረዳት ነኝ በሚሉ ግለሰብ ላይ ነበር:: እኚህ ሰው ቂጥኝ ያዘኝ ለሚል ሰው ሁሉ ፔንሲሊን የሰጡ በማስመሰል ወተት ይወጉ ነበር:: ታካሚውም መርፌ በመወጋቱ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ የዳነ መስሎት ይደሰት ነበር:: ሆኖም ግን ሲውል ሲያድር ከበሽታው አለመፈወሱ ሲያውቅ ማማረሩን ይቀጥላል:: ይህን ሁኔታ ቀኛዝማች ከአገሬው ሰምተው ክትትል አድርገው እውነት መሆኑን ሲደርሱበት ሳሙኤልን ጠርተው ከወቀሱ በኋላ ዳግም እንዳይለምዳቸው በማስጠንቀቅ አዲስ አበባ ለስራ በሄዱ ቁጥር ፔንሲሊን ይዘውላቸው ይመጡ ጀመር:: በእውነተኛው ፔንሲሊን ታክመው የዳኑት ሁሉ ፔንሲሊኑን ያመጡት ተካ መሆናቸውን ሲያውቁ የቀኛዝማች ውለታ ይሰማቸው ጀመር:: አገሬው ከቂጥኝ በተጨማሪ ያስቸግረው ከነበረው በሽታዎች መሃል ወባና ኮሶ ሌሎች ነበሩ:: ቀኛዝማች ለነዚህም የሚሆኑ መድኃኒት ከአዲስ አበባ እያመጡ ለሳሙኤል በሽያጭ ማቅረቡን ቀጠሉ:: ሆኖም ነጋዴ ትርፍ ያለው ነገር ስለሚያማልለው የመድኃኒቶቹን ትርፋማነት ሲገነዘቡ ለሳሙኤል መሸጡን ትተው ሱቃቸው ውስጥ ራሳቸው ለደንበኞቻቸው መሸጥ ጀመሩ:: አገሬው ከአዲስ አበባ ድረስ እቃ እንዲያመጡለት ሲጠይቅ ያለ ምንም የትራንስፖርት ክፍያ በማምጣት በቸገረው ጉዳይ ሁሌ ተሳታፊ በመሆናቸው የተነሳ ተካ የሚወደዱ ብቻ ሳይሆኑ የሚመለኩ አይነት ሰው ሆኑ::

ቀኛዝማች ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ለስራ ያላቸው ከበሬታ ወደር የለውም፡፡ ከብዙዎቹ ባህሪዎቻቸው አንዱ ቀኛዝማች የሚታወቁበት በሰዓት ቀልድ የለም በሚለው አቋማቸው ነው፡፡ ስለ ሰዓት ያላቸውን ከበሬታ ሲገልጹ «እኔ ሰዓት ከሚሰርቅብኝ ሰው ገንዘብ የሚሰርቀኝን እመርጣለሁ» ይላሉ፡፡ ስለዚህም የቀኛዝማችን እንቅስቃሴዎች በሙሉ ቤተሰባቸው ቀርቶ የጅማ ሰው ሁሉ ያውቀው ነበር ይባላል፡፡ ዕቃ ከአዲስ አበባ እንዲመጣለት የሚፈልግ ሰው መቼና በስንት ሰዓት ጅማ አይሮኘላን ጣቢያ ሄዶ እንደሚያገኛቸው ያውቅ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንግድ ትኬት ቢሮ ሳይቀር የቀኛዝማችን ቋሚ የጉዞ ኘሮግራም ስለሚያውቅ ትኬታቸውን ከመምጣታቸው በፊት አዘጋጅቶ ይጠብቃቸው ነበር፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ስናየው በደንበኛው ፍላጎት ላይ የተመሰረተው የመገበያያ ሰዓታቸው ለነዋሪው በሚሰጡት ከበሬታና ነፃ አገልግሎታቸው ሁሉንም የንግድ እንቅስቃሴያቸውን በተጠና አደረጃጀትና ወቅቱንና ሰዓቱን ጠብቆ የሚካሄደው እንቅስቃሴያቸው በአጋሮና በአካባቢው ገበሬዎች ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታን ከማስገኘቱ በተጨማሪ እሰየው የኛ ልጅ በማለት ግሪኮቹን በመተው የሳቸው ደንበኛ እንዲሆን አስቻለው፡፡ አጋሮ ላይ ከተራ ወኪልነት ተነስተው የሩቅ ግባቸው የሆነውን የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከውጭ ነጋዴዎች ቁጥጥር ነፃ የማውጣት ትግልን ሀ ያሉት ተካ በሁለት ዓመት ውስጥ ዘመቻቸውን ጅማ ድረስ በመሄድ ለመግጠም በስነልቦናም ሆነ በገንዘብ ዝግጁ ሆኑ፡፡

አጋሮ ላይ የፈጠሩት ዝና ቀድሞአቸው ጅማ ገብቶ ነበር፡፡ ሆኖም ተካ ሌላ ጉዳይ ገጠማቸው፡፡ አጋሮ ላይ ባገኙት ስኬትና ዝና ያልተደሰተው አንቶኒኖስ መተናኮሉን ይጀምራል፡፡ በአንድ ወቅት አቅመቢስና ልምድ የለሽ ወኪሉ የነበሩት ተካ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስኬታማ ነጋዴ መሆናቸውን ሲያውቅና ብዙ ሰዎች ተካን አድንቀው መናገር ሲጀምሩ በተዘዋዋሪ የራሱን ድክመት የሚያሳይ መስሎ ተሰማው፡፡ በዚህን ጊዜ ተካን ለማክሰር የማይፈነቅለው ድንጋይ ጠፋ፡፡ አንዴ የነበረውን ከፍተኛ የሀብታምነት ዝና በመጠቀም ከሀብታም የውጭ ነጋዴዎች ጋር በሽርክና መስራትን እንደ ክብር ከሚመለከቱ አትዮጵያዊያን ባለስልጣኖች ጋር በመተባበር ገንዘቤን ሰርቆኛል በማለት አዲስ አበባ ውስጥ አሳሰራቸው፡፡ ቀኛዝማች ምንም እንኳን ጥፋት እዳልሰሩ ቢያውቁም እስር ቤት ከመታሰር አጥፍቻለሁ በማለት ከእስር በመፈታት ንግዳቸውን መቀጠሉ የሚያዋጣ መሆኑን በማወቅ ይቅርታ በመጠየቅና የተባለውንም ገንዘብ እንደሚከፍሉ ቃል በመግባት ተፈቱ፡፡ ያሉትንም ፈፀሙ፡፡ አንቶኒኖስ አሁንም የአንድ እዚህ ግባ የማይባል ወጣት ኢትዮጵያዊ የንግድ ድልን በነጮች ላይ እንደተቃጣ ጥቃት በመቁጠር እሳት የላሰ ነጋዴ ነው የተባለ ግሪካዊ በመመልመል የሚያስፈልገውን ሁሉ ድጋፍ በመስጠት ጅማ ድረስ ላከባቸው፡፡ ሆኖም ግሪኩ የንግድ ችሎታው ሳያንሰው የካርታ ሱስ ስለነበረበት ጊዜውን ካርታ በመጫወት ሲያሳልፍ ጠንቃቃና ስኬታማው ተካ በኪሳራ ጅማን ለቆ እንዲወጣ አደርጉት፡፡ ከስህተቱ አልማር ያለው አንቶኒኖስ ከጊዜ

*ወደ ጊዜ ሲከስር ቆይቶ በመጨረሻ ላይ በ1966 ዓ/ም አብዮት ሲነሳ ኢትዮጵያን ጥሎ ወደ አገሩ ቢመለስም እዛ በደረሰበት ችግር ራሱን ገደለ፡፡*

*በ1945 ዓ/ም አካባቢ ጅማ ውስጥ የጠጅ ቤት ባለቤት የሆኑትንና ውቢቷን ወይዘሮ ደጊቱን በደመቀ ጋብቻ በማግባት ቀኛዝማች የእድሜ ልክ ትዳራቸውን መሠረቱ፡፡ ሁለቱም ተጋቢዎች ጅማ እምብርት ላይ የነበረውን ጠጅ ቤት ወደ ተካ ሆቴልነት ለወጡት፡፡ በዚህ ወቅት አጋሮ ላይ የጀመሩትን የውጭ ነጋዴዎችን ከመጠጥ ንግድ የማስወጣት ትግል ጅማ ላይ ቀጥሎ ነቅነቅ የማይሉ የዘርፉ ቁጥር አንድ ነጋዴ ሆኑ፡፡*

*በወቅቱ ጅማ ውስጥ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ያከፋፍሉ የነበሩት አንቶነሊ እና ዳንኤሊ የተባሉ ጣልያኖች ነበሩ፡፡ ተካ እኔም ላከፋፍል ቢሉ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካ ሃላፊዎች ልጅነታቸውን በመመልከት ከገንዘብም ገንዘብ ከችሎታም ችሎታ አይኖረውም በማለት ከለከሉአቸው፡፡ ቆየት ብለው ግን የማከፋፈል ዕድሉን ሰጧቸው፡፡ ከፈረንጆች ባነሰ ዋጋ በማከፋፈልና በዘመኑ አግባብ በነበራቸው የተለያዩ የብልጠት የማስታወቅያ ስራዎች በማሰራት ጣልያኖችንና በጅማ ከፍተኛ ተወዳጅነት የነበረውን መሎቲ ቢራን ከገበያ ማስወጣት ብቻ ሳይሆን ከአዲስ አበባ እስከ ጐሬ፣ ከደሴ እስከ አሰብ፣ በምስራቅ ኢትዮጵያ ደግሞ ጅቡቲን ጨምሮ ከድሬደዋ እስከ ጂጂጋ ያለውን ተቆጣጠሩት፡፡*

*በማከፋፈልና የሆቴል ንግድ ዘርፍ በመግባት ከፍተኛ ሀብትና ንብረት ካፈሩ በኋላ ወደ አግሮ ኢንዱስትሪ የንግድ ዘርፍ በመግባት የሚሸጡትን ዕቃ ወደ ማምረት ገቡ፡፡ ከ1947 ገደማ ጀምሮ በጊቤ አካባቢ ላይ በቡና ተክል ላይ መዋዕለንዋያቸውን ማፍሰስ ጀመሩ፡፡ ስለ ዘመናዊ እርሻ ያላቸውን ልምድና ዕውቀት ውስኑነት በደንብ የሚያውቁት ተካ በዚህ የንግድ ዘርፍ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል ሀብት እና እውቀት ያላቸውን ሰዎች አብረዋቸው እንዲሰሩ መገፋፋትና ማስተባበር ጀመሩ፡፡ በዚህ የተነሳም በ1950 አካባቢ ጋላንቲኒ ከሚባል ጣልያናዊ ከበርቴና የሳሪስ ወይን ጠጅ ባለቤት ከነበረው አሌክሳንድራኪስ የሚባል ግሪካዊ ጋር በመተባበር የአግሮ ኢንዱስትሪ ካምፓኒ መሠረቱ፡፡ የካምፓኒውን መዋጮ የአንበሳውን ድርሻ የጨበጡ እንደመሆናቸው ድርጅቱ ተካ ኤገኖና ካምፓኒው በማለት ተሰየመ፡፡ በ*150,000 *ብር የተቋቋመው ካምፓኒ ጌራ እና ዶዮ ላይ ከካፒታሉ የተወሰነ ገንዘብ በማውጣት 490 ሄክታር መሬት በመግዛት ስራውን ጀመረ፡፡*

*በ1961 ዓ.ም የሽሪኮቻቸውን ዕጣ በሙሉ በመግዛት ካምፓኒውን የግላቸው አደረጉት፡፡ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ የነበረውን አናስታሲዮ የተባለው ጣልያናዊ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅነቱን እንዲቀጥል በማድረግ ስራውን ገፉበት፡፡ ካምፓኒው 200 መቶ ቋሚ ሰራተኞች የነበሩት ሲሆን በምርት ወቅት ተጨማሪ 600 ጊዚያዊ ሰራተኞችን ይቀጥር ነበር፡፡ የቀኛዝማች እርሻ በወቅቱ በአካባቢው ከነበሩት የተለየና በእጅጉ የላቀ ነበር፡፡ እርሻውን ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል*

1ኛ እርሻው የተደራጀውና ይመራ የነበረው ዘመናዊ የእርሻ እንዱስትሪዎች መከተል ባለባቸው የፋይናንስ የአስተዳርና ቴክኒካዊ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑ ነው።

2ኛ የእርሻው የአመራረት ጥራት በዘርፉ ኤክስፐርቶችና በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ዕውቀት ከነበረው የኦክሎሆማ ዩኒቨርስቲ ዕውቅና የተሰጠው ከመሆኑ በተጨማሪ ዩኒቨርስቲው በሙያው ላይ ጥናት የሚያካሂዱ ምሁራን እና ተማሪዎች በመላክ በእርሻ ድርጅቱ ውስጥ ምርምር እንዲሰሩ በማድረጉ ነው።

3ኛ የዓለም ባንክ ለኢትዮጵያ ብድር እንዲፈቀድ ሲፈለግ እንደ ሞዴል ዘመናዊ አግሮ ኢንዱስትሪ በመውሰድ የዓለም ባንክ ባለስልጣኖች ይጎበኙትና ይሁንታቸውን እንዲሰጡ መንግስት ይጠቀምበት የነበረ ድርጅት መሆኑ ነው።

4ኛ በአካባቢው ከነበሩት መሰል የእርሻ ካምፓኒዎች በተለየ መልኩ ምርታማና አትራፊ መሆን የቻለው በትንሽ ሰራተኛ ብዙ ማምረት በመቻሉ ነው። ይኸውም ካምፓኒው ለሰራተኛው የሚከፍለው ከመሰል ድርጅቶች ጋር ሲነጻጸር ትንሽ ነው። ሆኖም ሠራተኞች የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን ያገኙ ስለነበር በሙሉ አቅማቸው ለማምረት ዝግጁ ነበሩ።




*የቀኛዝማች ተካ ኤገኖ እርሻ በወጣቶች ሲጐበኝ*

## ካምፓኒው ለሰራተኞች ይሰጥ ከነበሩት ጥቅማጥቅሞች

1. ምቹ የመኖሪያ ቤቶችና የገላ መታጠቢያ የመሳሰሉ አቅርቦት ለሰራተኛው በነፃ ያቀርባል፡፡
2. መሰል ድርጅቶች ለሰራተኞቻቸው የበቆሎ ዱቄት ሲያቀርቡ የቀኛ ዝማች ድርጅት ግን ለሰራተኞቹ እንጀራ በወጥ በማቅረብ ምግብ ለማዘጋጀት የሚያባክኑትን ጉልበት በመቆጠብ ስራ ላይ እንዲያውሉ ያደርግ ነበር፡፡
3. ሰራተኞች ጠንካራና የበለጠ አምራች እንዲሆኑ ለማድረግ ንጋት ላይ ከእንቅልፋቸው በመቀስቀስ የአካል እንቅስቃሴ ስፖርት እንዲሰሩ ይደረጉ ነበር፡፡
4. ሰራተኞች በአካባቢው ከፍተኛ የጤና ዕክል ይፈጥር በነበረው የወባ በሽታ ተጠቅተው ከስራ እንዳይስተጓጎሉበት በነፃ የወባ መከላከያ ያድል ነበር፡፡


ቀኛዝማች በደንብ የተደራጀ የተሟላና የተቀላጠፈ አስተዳደር በመፍጠር ውጤታማ የእርሻ ድርጅት በማቋቋማቸው፤ በሌላ አነጋገር በምዕራብ ኢትዮጵያ ውስጥ በዘመናዊነት ወደር የሌለው ሜካናይዝድ የእርሻ ካምፓኒ በማቋቋማቸው የተነሳ በ1957 ዓ/ም በወቅቱ በአገሪቱ ከፍተኛ ክብርና ዝና የነበረውን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት በእርሻ ዘርፍ የወርቅ ሜዳልያ ለመሸለም በቅተዋል፡፡



*ቀኛዝማች ተካ የቀ.ኃ.ሥ. ሽልማትን በተቀበሉበት ወቅት*

በ1965 ዓ/ም ላይ ከጅማ ከተማ 73 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው ጎጀብ አካባቢ የራስ መስፍን ሁለት ልጆችና የራስ መስፍን እህት ይዞታ የነበረውን 60 ጋሻ መሬት ገዙ፡፡ ይህ ለእርሻ የሚሆነውን

*ውኃ በቀላሉ ከጎጀብ ወንዝና በአካባቢው ከሚገኙ አራት ገባር ወንዞች ያገኝ የነበረ ለምና ምርታማ መሬት ነበር፡፡ በዚህ መሬት ላይ ቀኛዝማች ያመርቱ የነበረው በቆሎ፣በርበሬ፣ጥጥ፣አናናስ፣ብርቱካን እና ሶያቢንስ ዋናዎቹ ነበሩ፡፡*



*የቀኛዝማች ተካ ኤገኖ እርሻ በባለሥልጣናት ሲጎበኝ*

*ከዚህ በተጨማሪ መጀመሪያ ላይ ከጣልያን ሸንኮራ አገዳ መጋዘን በመግዛት ሸንኮራ ቸርቻሪ የነበሩት በመቀጠል የሕንድ ገንዘብ ምንዛሬ ተላላኪና የግሪክ መጠጥ ፋብሪካ ባለቤት ወኪል በመሆን ንግድንና ኢትዮጵያዊነትን በስኬት ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ ሲታገሉ ያደጉት ተካ አጋሮና ጅማ የነበሩትን የውጭ ነጋዴዎች አሸንፎ ከንግድ ውጭ በማድረግ ያገኙትን ድል ድሬዳዋ ላይ በመድገም የፈረንጅ ወኪል ከመሆን አልፈው ፈረንጅ ቀጥረው ማሰራትን እንደ ግብ ሳይቆጥሩ አገሪቱ ውስጥ በአግሮ እንዱስትሪው መስክ ከፍተኛ ዝና ካላቸው ከተንዳሆ ጥጥ ተክልና ወንጂ ስኳር ጋር ለመወዳደር ቆርጠው ተነሱ፡፡ በዚህ የተነሳ ከአንድ የአሜሪካ የንግድ ድርጅት ጋር በመተባበር የታሸጉ የአናናስ ምርቶችን፣ የቲማቲም ድልህና ጭማቂ የመሳሰሉ በማምረት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ተዘጋጁ፡፡ ሆኖም ምን ይደረግ የ1966ቱ የደርግ መንግስት መጥቶ ባጭር የተቀጨ ጉዞ አደረገው፡፡*



*ቀ/ተካ ኤገኖ የቀ.ኃ.ሥ. ሽልማትን በማግኘታቸው ጓደኞቻቸው ቀ/ሞላ ማሩ (በግራ በኩል) ቀ/ተመስገን ኤርሰዶ (በቀኝ በኩል) የወርቅ ሰዓት ሲያበረክቱላቸው (1957 ዓ.ም)*

ከዚህ በተጨማሪ በ1964 ዓ/ም 800,000 ብር በማውጣት በጅማ ከተማ ታሪክ የመጀመሪያውን ዘመናዊ ሆቴል ከፍተዋል፡፡ ሆቴሉንም ለሚወዱአቸው ባለቤታቸው መታሰቢያ እንዲሆን ደጊቱ ሆቴል ብለው ሰይመውታል፡፡ ሆቴሉ ካሟላቸው ዘመናዊ ዕቃዎች በተጨማሪ እንደሳቸው ሁሉ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት በስዕል ዘርፍ አሸናፊ የነበረው የሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታን ስዕል ያካተተ ነበር፡፡

ደርጎች በ1966 ዓ/ም ስልጣን ሲይዙ ተካና እሳቸውን የመሰሉ ጥረው ግረው ሀብት ያፈሩ ሳይቀሩ ለሞትና ለእስር ተዳረጉ፡፡ ድህነትን ታግለው ያሸነፉት ተካ ኢትዮጵያዊነትን በወሬ ሳይሆን በተግባር ክብር ያላበሱት ተካ በደርግ መንግስት «የሰፊው ሕዝብ ጠላት» የጭቁኑ ደም መጣጭ»፣ «የኢምፔሪያሊዝም ቡችላ» ተብለው ዘብጥያ ወረዱ፡፡ ሁለት ጊዜ ታስረው ፍዳቸውን አዩ፡፡ እስር ቤት ውስጥ ስህተትህን አጋልጥ የሚለው ተደጋጋሚ ዛቻ ሲበዛባቸው «አዎ አንድ ስህተት ፈጽሜአለሁ እሱም እኩዮቼ የሆኑት የውጭ ነጋዴዎች ሀብታቸውን ውጭ አገር ሲያከማቹ እኔ ግን አገሬ ነው በማለት እዚህ አስቀምጬ ለናንተ ማስረከቤ ነው» በማለት መለሱ፡፡ ቀኛዝማች የደርግ ዘመንን አጥብቀው የሚጠሉት ሀብትና ንብረታቸውን ስለቀማቸው ብቻ ሳይሆን እንዳይሰሩ ስለከለከላቸውም ጭምር ነው፡፡

በእርግጥ ቀኛዝማች አብዮቱ እንደፈነዳ አልነበረም ለእስር የተዳረጉት ያ ንግድን አቀላጥፎና ከሌሎች በልጠ በመገኘት ለከፍተኛ ስኬት ያበቃቸው ብሩህ አእምሮ በአደጋ ጊዜም እሳቸውን ለመታደግ

ረድቶአቸዋል፡፡ ወቅቱ እያንዳንዷን ሁኔታና እርምጃ በጥንቃቄና በብልሃት ያልተራመደ ታዋቂ ሰው ባልታሰበ ቅፅበት ህይወቱን የሚያጣበት አጋጣሚ ብዙ ስለነበረ ራስን ከአደጋ ለመጠበቅ ንቁና ፈጣን መሆን የግድ ነበር ፡፡ ቀኛዝማች ራሳቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ የወሰዱት እርምጃ ራሳቸውን ተስፋ የቆረጠና የባዘነ ሰው አስመስሎ በመታየት ከጠላቶቻቸው ጥቃት ለማምለጥ ዘየዱ፡፡

ለዚህም ሲባል ወዳጃቸው ከሆኑት አቶ እየሱስ ወርቅ ዛፉ ፒፓ በመዋስ ትምባሆ ማጨስ ጀመሩ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቻይና አገር ስሪት የሆነና በወቅቱ የአብዮቱ ተከታዩች ያጠልቁት የነበረ ኮፍያ በማድረግና የታችኛው መደብ አባሎች ይለብሱት የነበሩትን ልብሶች በመልበስ ስራፈቱና ባዘኔው በሚዝናኑባቸው ቦታዎች በመሄድ ቁማር በመጫወትና መጠጥ በመጠጣት ጊዜያቸውን ማሳለፍ ጀመሩ፡፡ በዚህ የተነሳም በወቅቱ እንደጦር ይፈሩ የነበሩት የደርግ ባለስልጣኖችና ከድሬዎቻቸው እሱኮ ተራማጅ ሆኖአል ጠጪም ብኩንም ሆኗል በማለት ችላ አሏቸው፡፡

ይህ ዘዴያቸው ግን መዝለቅ የቻለው እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ነበር፡፡ በ1971 ዓ.ም. ከውርስ ከተረፈው ተካ ሆቴል ሰራተኞች ጋር በተፈጠረው የአሰሪና ሰራተኛ ውዝግብ የተነሳ ቀኛዝማች ችላ ብለዋቸው በነበሩት ባለስልጣናት ትኩረት ውስጥ ገቡ፡፡ ሠራተኞቻቸው ባቀረቡባቸው የተለያዩ የሃሰት ክሶች የተነሳ በቀጥታ ወደ እስር ቤት ተወረወሩ፡፡ በወቅቱ የጅማ ክፍለ ሀገር የደርግ ተጠሪ የነበሩት ተሰማ በላይ "እስካሁን ድረስ ይህን የመሰለ አደገኛና በዝባዥ አድሃሪ ለእስርና ለቅጣት አለመብቃት አብዮታችን ከፈጸማቸው ስህተቶች አንዱ ነው፡፡ ተገቢውን ምርመራ ተካሂዶበት የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ የአብዮቱን ደህንነትና የወዛደሩን መብት ማስከበር አለብን" በማለት ለበታቾቻቸው ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡

ተሰማ በላይ ተካን የአብዮቱ አደገኛ ጠላት አድርጎ በማቅረብ የሞት ፍርድ እንዲፈፀምባቸው ለማድረግ የሃሰት ክሶችን አቀረቡ፡፡ ከቀረቡት ውንጀላዎች ውስጥ የራስ መስፍን ስለሺ ቤት ሲፈተሽ ምንም ዓይነት ገንዘብ ሳይገኝ በቀኛዝማች ቤት ውስጥ ግን ስምንት ሚሊዩን ብር ተደብቆ እንደተገኘ በማስመሰል ክስ መሰረቱ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አብዮቱን በትጥቅ ለመፋለም ቀኛዝማች ባላቸው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ ሶስት የጦር ሜዳ መሳሪያ በድብቅ አስቀምጠው እንደነበረና በፍተሻ እንደተገኘባቸው በማስመሰል ክስ መሠረቱ፡፡ "በአጠቃላይ የመደብ ጀርባቸው ሲታይ የወዛደሩን ላብና ጉልበት በመበዝበዝ ከፍተኛ ንብረት ያፈራ የአብዮቱ ቀንደኛ ጠላት ከመሆናቸው በተጨማሪ አድሃርያን ከመጠን ያለፈ ሃብትና ንብረት በአዋጁ መሰረት እንዲያስረክቡ ግዴታ እንዳለባቸው እያወቁ ከመጠን ያለፈ ሃብት በቤታቸው መደበቃቸው ላይ ናቸው፣ አብዮቱን በጦር መሣሪያ በመውጋት በብዙ ጓዶች መስዋእትነት የተገኘውን አብዮት ለመቀልበስ የተነሳሱ በዝባዥ ቡርዦዋ ስለሆኑ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው አሳስባለሁ" በማለት ጓዶቻቸውን አሳመኑ፡፡

ቀኛዝማች ተካ ግን ከሞት የታደጋቸውን ምስክርነትና ድጋፍ ያገኙት በምንም ዓይነት መልኩ ካልገመቱትና ካልጠበቁት ቁንጮ ባለስልጣን ነበር:: ቀኛዝማችን ከሞት የታደጉት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ናቸው:: ኮሎኔል መንግስቱ በቀጥታ ተሰማ በላይን በስልክ በማግኘት "ምንም ዓይነት እድፍ ያልተቀላቀለበት ኢትዮጵያዊ "ስለሆነ አደጋ ብታደርስበት ውርድ ከራሴ ነው በማለት ተግሳጽ የታከለበት ትዕዛዝ ስላስተላለፉ ነው ከእስር የተፈቱት:: ቀኛዝማች ከኮሎኔል መንግስቱ ጋር ስለነበራቸው ትውውቅ ሲናገሩ "የኮሎኔሉ አጎት የሆኑት አስራት ወልዴ በተካ ጋባዥነት መኖሪያ ቤታቸው እራት ከሚጋበዙ ጥቂት ሰዎች አንዱ ነበሩ:: የአስራት ወልዴ ወንድም ልጅ የሆኑት ወጣት መኮንኑ መንግስቱ ኃይለ ማሪያምም ወደ ሰባት ጊዜ አጎታቸውን ተከትለው እየመጡ ተካ ቤት እራት ተጋብዘው ነበር::" መንግስቱ የጅማ ሰው እንደመሆናቸው ስለቀኛዝማች ተካ ማንኛውም የከተማውና ያከባቢው ሰው ከሚያውቀው በተሻለ ሁኔታ እንዲያውቋቸው ያስቻላቸው በእራት ግብዣዎቹ ጊዜያት ከቀኛዝማች ጋር በአካል በመገናኘት እራት እየበሉ በእርጋታና በመዝናናት ባደረጓቸው ጭውውቶች የተነሳ ነው::

ቀኛዝማች ከእስር ተለቀው የኢህአዲግ መንግስት ደርግን ከስልጣን እስካስወገደበት ድረስ በነበሩት ዓመታት አብዛኛውን ጊዜያቸውን ያለ ስራ ያሳለፉት የነበረው አዲስ አበባ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ነበር:: በደረሰባቸው ከፍተኛ የንብረትና የሃብት ውርስና ባስከተለባቸው ከፍተኛ የህሊና ጠባሳና እስር ከምንም ነገር በላይ ከሚወዱት ስራ ፈጠራ ከመለየታቸው የተነሳ አስራ ሰባቱን የአብዮት ዘመን ከዓለም ጋር እንደተጣላ ሰው ከብዙ ነገሮች በመገለል በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንደ ቁም እስረኛ ነበር ህይወታቸውን የገፉት::

ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ግን እንደ አዲስ ሀ በማለት በአዲስ ጉልበትና ከፍተኛ ፍላጎት የንግዱንና የስራ ፈጠራውን ዓለም ተቀላቀሉ:: በፊት ወደለመዱትና ስኬታማ ወደሆኑበት የመጠጥ ማከፋፈል የንግድ ዘርፍ ፊታቸውን በመመለስ የበደሌ ቢራ አከፋፋይ ሆኑ:: ሆኖም የበደሌ ፋብሪካ ሀላፊዎች ፈፀሙብኝ በሚሉት በደል የተነሳ በደረሰባቸው ኪሳራ ስራውን ተውት:: በመቀጠል የቻይና ስሪት የሆነው የጂፋንግ መኪናዎች አስመጪ ሆኑ:: ከቻይናዎቹ ጋር የተጀመረው ንግድም ስኬታማ ሳይሆን ቀረ:: ቀኛዝማች ስለሁኔታው ሲናገሩ "በደሌዎች በደል ፈፅመውብኝ ከሰርኩ:: ከቻይናዎች ጋር መስራት ደግሞ አዳጋች ነው:: በመጨረሻ ሁለቱም በክርናቸው ስለደቆሱኝ በኪሳራ ንግዱን ዘጋሁ" ይላሉ::

ሆኖም እንደሁሌው ወድቆ መነሳቱን ስለሚያውቁበት በአሁኑ ወቅት ስኬታማና ትርፋማ በሆነ ንግድ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ:: ጅማ ከተማ ውስጥ በቀላጤ ተወርሶ የነበረውን ደጊቱ ሆቴል የኢህአዴግ መንግስት ሲመልስላቸው:: ሆቴሉን እንደ አዲስ በማደራጀት፣ በማደስና አዳዲስ አገልግሎቶች እንዲሰጥ በማድረግ በከተማው ውስጥ ትርፋማና ዘመናዊ ሆቴሎች ተርታ ለማሰለፍ

አብቅተውታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በደርግ መንግስት ያልተወረሰው ተካ ሆቴልም ስኬታማ ነው፡፡ አሁን በቅርቡ ደግሞ ከ PVC የሚሰራ ማለትም እንጨት መሰል የሆኑት ለኮርኒስና፣ ክፍሎችን ለመከፋፈል የሚያገለግል ቁሳቁስ የሚያመርት ፋብሪካ በማቋቋም በኢንዱስትሪው የንግድ ዘርፍ ውስጥ ተሰማርተዋል፡፡ ቀኛዝማች አሁንም በዕድሜ ብዛት የጤና መታወክ ገጥሟቸው በሐኪም ትዕዛዝ እረፍት እንዲያደርጉ ቢነገራቸውም የሃይማኖትን ያህል ከሚያመልኩት ስራ ላለመነጠል ሲሉ የሐኪሙን ትዕዛዝ ችላ በማለት ቀኑን ሙሉ ፋብሪካቸው ውስጥ ደፋ ቀና ሲሉ ይውላሉ፡፡ ቀኛዝማች ሐኪም የነገራቸውን እንዲፈፅሙ ቢነገራቸው የሚሰጡት እጭር መልስ "እጄን ሳልንተራስ ከስራ የሚለየኝ የለም" የሚል ነው፡፡

* * *

## በውይይት ወቅት የቀረቡ ጥያቄዎችና አስተያየቶች

**ጥያቄ፡-** *እንዲህ አይነቱን አባት ባለማወቁ በጣም እራሴን ወቅሻለሁ፡፡ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ እንዲህ አይነቱን ሥራ መስራቱ ሊያስመሰግነው ይገባል፡፡ ይህ ታሪክ ነውና ለልጅ ልጅ ሊተላለፍ የሚችል ነው፡፡ በቀጣይነት አሁን ቀኛዝማችን አብሯቸው የሚከተላቸው ሌላ ሠው አለ ወይ? እናንተም እንዲህ አይነቱን ነገር መድረክ ላይ ማቅረባችሁ ጐሽ ተባረኩ የሚያሰኝ ነው፡፡ እኔ እዚህ አዳራሽ ያሉትን ታዳሚዎች አላውቅም፤ ግን ተነስተን እንደው አድናቆታችንን ብንገልፅላቸው እወዳለሁ፡፡ (ጭብጨባና ታዳሚው ተነስቶ አድናቆቱን ገለጸ) እግዚአብሄር ይሰጥልኝ፡፡ የመጣሁት ከአገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው፡፡ በሙያዬ ኢኮኖሚስት ነኝ፡፡ አልሠራሁበትም፡፡ በእውነት ከኔ በኋላ ምን ትሆናለች ኢትዮጵያ፤ ባለቤት አላት ወይ--- በተለይ ፊልሙ ለተማሪዎች፣ ለልጆቻችን ሊያገለግል ስለሚችል የድምፅ አቀራረፁ ተሟልቶ ቢቀርብ እወዳለሁ፡፡ ቀጣይነት እንዲኖረው ከቀኛ ዝማች ስር እየተተካ ያለ ወገን አለ ወይ? አመሠግናለሁ!*

**ጥያቄ፡-** *እሺ የተጠየቀውን ጥያቄ ለማዳበር ነው የፈለኩት፤ ምክንያቱም በልቤ የነበረ ጥያቄ ነው፡፡ ከልጆች የሚተኩአቸው አሉ ወይ? ሴቶች ልጆችስ አሉ ወይ? ባለቤትዎ በእርግጥ ታታሪ ሴት መሆናቸው ይሠማል፤*

**ጥያቄ፡-** *እንደ ጋዜጠኛ ሣይሆን እንደ ማንኛውም ሠው ልጠይቃቸው ፈልጌ ነው፡፡ አባባ ተካ ወይም ቀኛዝማች እንኳን ለዚህ ጊዜ ደርሠው ከአንደበትዎ አንዳች ነገር ለመስማት ደግሞ እኛ ስለታደልን እግዚአብሔር ይመስገን እንኳን አደረሰዎት ብዬ ነው በቅድሚያ የምለው፡፡ እንደው ሌላ ነገር አይደለም ሠው ችግር ሲገጥመው ችግሩን ተጋፍጦ ለማለፍ ጥረት በሌለበት በማይታሠብበት ዘመን ውስጥ ነው ያለነው፡፡ እናም እንዲመልሱልኝ የምፈልገው ወድቆ መነሳትን ከማን ተማሩ? እንዴት ነው የሚያጋጥምዎትን ችግርና ፈተና - ባዶ እጅ መቅረት፤ እንደገና ደግሞ ተጣጥሮ ብድግ ማለት - ከማን ወረሱት? ሌላው ሠው እንዴት አድርጎ ፈተናን እንዲቋቋም ይመክራሉ? እዚህ ላይ የእርስዎን አስተያየት እፈልጋለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡*

**የቀኛዝማች ተካ መልስ፡-** *እኔ ለዚህ በቅቼ ለመናገር በመብቃቴ በጣም አመሠግናለሁ፡፡ መጀመሪያ የተጠየኩት ጥያቄ አለ እንደተጠየቀው እኔን የሚተካ አለ ወይ? አዎ ልጆች አሉ፡፡ እኔ ስሰራ ለልጅ ለወራሽ ብዬ አይደለም፡፡ አንደኛ ለራሴ ነው፡፡ ሁለተኛ ለሀገር ነው፡፡ ብዙ ነገር የሠራኂቸዉ ነገሮች በእርሻው በምኑ ... ያፈራኂቸው ነገሮች ለሀገር እንዲሆኑ እንጂ ለእራስ ብቻ አይደለም፡፡ ልጆች አሉ ሁሉም ለየራሳቸው*

ይጥራሉ፡፡ እርግጥ ከሠራኋቸው ነገሮች ሁሉ ለሃገር የሚጠቅም ነገር እንዳለ ብዬ ነው የምሰራው ለምሳሌ እርድ ወደ ኢትዮጵያ ያስገባሁት እኔ ነኝ፡፡ እርድ በኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም፡፡ ሶያ ቢን ያላገባሁኝ እኔ ነኝ፡፡ እኔ የምሰራው ስራ በእውነቱ ለሀገር፤ ለራስም የሚጠቅም ነው፡፡ ልጆች አሉ የየራሳቸው ስራ እየሰሩ ነው፡፡ በእውነቱ በሀሣቤም ለልጅ ለምን የምል ሣልሆን ጠቅላላ ለሃገር የሚሆን ነገር ነው የምሠራው፡፡ በምሠራቸው ብዙ ነገሮች ውስጥ ገብቼ ወደፊት ምናልባት እዘረዝረዋለሁ፡፡ ለአሁኑ ጥያቄ ይህ ይበቃል፡፡



የውይይቱ ታዳሚዎች

መቼም በእውነቱ ሥራ ሁልጊዜም መሥራት ነው፡፡ ለምሣሌ ድህነትና ብልጽግና ስንፈጠር አልነበረም፡፡ የሰው ልጅ ሲፈጠር ስንፍናና መስራትን ነው የፈጠረው፡፡ ድህነት ስንፍናን ይወልደዋል፡፡ ብልጽግና መስራትን ይወልደዋል፡፡ ድህነትም እንደዛው፡፡ (የሞቀ ጭብጨባ) ሠው ደግሞ ከሠራ ሁልጊዜም የሚቸግረው ነገር የለም፡፡ እና እኔ በእውነቱ ሥራ እወዳለሁ፡፡

እኔ ስራ የጀመርኩበትን ጊዜና ወደዚህ የመጣሁበትን ቀን አስታውሳለሁ፡፡ በሦስት አመቴ አገልግሎት ላይ የዋልኩበት ቀንና ሠው መሆኔን ያወኩበት ቀን ነበር፡፡ እናቴ ወደ ወንዝ ስትሄድ የሦስት አመት ልጅ ነበርኩ፡፡ ታናሽ ወንድሜ ደግሞ አናቱ ላይ ቅቤ ይደረግለታል፤ እጠብቃለሁ፤ ቁጭ ብያለሁ፤ ጥቁር እባብ ይመጣና ያችን ቅቤ እየበላ ይሄዳል፡፡ አሁን እንግዲህ አንደኛ እባብም አዋቂ ነው ወይ? ትልቅ ሠው

መኖሩን ያለመኖሩን ያውቃል ወይ ብዬ፤ እቤት ትልቅ ሠው አለመኖሩን ያውቃል እናቴ እንስራ ይዛ ስትወጣ ያያታል እኔ አላየውም መጥቶ ሲልስ ብቻ ነው፡፡ ታዲያ ሠው መሆኔን ያወኩኝና በሥራ ላይ መሆኔን ያወቅኩት ያ እባባ መጥቶ ቅቤ ልሶ ሲሄድ ነው፡፡ በኋላ መንገር አልችልም ይመጣል፡፡ እኔም ዝም እላለሁ፡፡ በኋላ ተደረሠበትና ወገርት የሚባል ነገር ይታጠናል:: ማን አግኝቶበት፣ በዛው ሄደ፡፡ ከሦስት አመት ጀምሬ አገልግሎት ሠጥቻለሁ፡፡ ( ሞቅ ያለ ጭብጨባ … )

አስተያየት፡- ያባታችንን የቀኛዝማችን ታሪክ በሚስብና በሚገባ ቋንቋ አቀነባብረው ያቀረቡትን ወንድማችንን እጅግ በጣም አመሠግናለሁ፡፡ (ሞቅያለ ጭብጨባ) የነዚህ አይነቶቹን ሰዎች ታሪክ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ቀምሮ በማቅረቡ፡፡ አሁን እኛ ሰምተንዋል፡፡ እርግጠኛ ነኝ ይሔ ነገር በጽሁፍ ሆኖ ለትውልድ ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ከጽሁፋቸው ውስጥ እጅግ በጣም የማረከኝ ደግሞ ከአባታችን ታሪክ ጋር የምኒልክን አዋጅ ከእሳቸው ታሪክ ጋር አጣጥሞ ማቅረቡ ነው፡፡ እና ለዚህ ሁሉ ቅንብር የደከሙትን ፀሐፊ ለማመስገን ነው፡፡

ጥያቄ፡- እኔም አመሠግናለሁ፡፡ በህይወት እያሉ እሳቸው እየሰሙ ታሪካቸውን አብረን ስለሰማን በጣም ነው የተደሰትኩት፡፡ ሠዎች ካለፉ በኋላ ነው ታሪካቸው የሚነገርላቸው፤ እድለኛ ናቸው በህይወት እያሉ ታሪካቸውን አብረውን መቋደሣቸው፡፡ ነገር ግን ታሪክ ተራኪው ለውጥ ላይ አደረሰንና ከለውጥ በኋላ የባለ ታሪኩ ህይወት እንዴት እንደሆነ አንጠልጥሎን አስቀረን፡፡ እንዴት ሆኑ? ከዛ በኋላ እንዴት ተነሱ? አሁን ካሉበት እንዴት ደረሱ? አመሠግናለሁ፡፡

ጥያቄ፡- ከቀኛዝማች ተካ ጋር እንደታላቅ ወንድም ነን፡፡ በጣም የማደንቃቸው ናቸው፡፡ እና ብዙም አልናገርም፡፡ በግል አውቃቸዋለሁ፤ በጣም ከማደንቃቸው ሠዎች መካከል ናቸው፡፡ እኔ አንድ ነገር ለመጠየቅ ፈልጌ ነው የተነሳሁት፡፡ ቀኛዝማች ሀብት በመፍጠር ዙሪያ በጣም ጉልሕ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ቀኛዝማች ግልፅ በመሆናቸው እኔ አንድ ነገር የምጠይቀው አለኝ፡፡ ብር የማባከን ባህል በሀገራችን በጣም በሰፊው የሚታይ ነው፡፡  በዚህ ዙሪያ ቀኛዝማች የሚሠጡን አስተያየት ካለ፡፡ ሀብት እየተካበተ እንዲመጣና ስለ መቆጠብ ስለ አለማባከን እና በቁም ነገር ላይ መልሶ መላልሶ ስለ ማዋል የሚመክሩን ነገር ካለ ጥሩ ይሆናል የሚል ግምት አለኝ፡፡

የቀኛዝማች ተካ መልስ፡- ለውጥ እንደመጣ መቼም - ለውጥ መጣ ማለት በእውነት እንደው ለውጥ ለማለት ብቻ አይደለም፡፡ እንግዲህ ስራ ስሩ የሚል፤ የሚሸልም፤ የነበረውን የሚያበረታታ ቀርቶ ለውጥ

እንደመጣ እንግዲህ አድሃሪ፣ አቆርቋዥ፣ በራዥ፣ ከላሽ፣ እ..እ የሠርቶ አደር ቁጥጥር አድሃሪ … ምኑ በቃ… ያ የመስራት ነገር ተጠናቀቀ። በእውነት አሁን ሠውነትን ማዳኛ ግዜ ነው። በዛን ግዜ እኔ ምንድን ነው ያደረግኩት፤ ሥራቸው ይወስዳሉ፣ ይወስዳሉ፤ በእውነት ውርስ ከደረሠበት ሰው በኢትዮጵያ ትልቁ እኔ ነኝ። ትልቅ ውርስ፤ ይሄን ይወርሳሉ ይታወጃል፤ ይሄን ይወርሣሉ ይታወጃል፤ ያን ግዜ ብዙ ድርጅት ነበረኝ። በኋላ እንግዲህ ቢቸግረኝ ከእየሱስ ወርቅ ዛፉ አንዲት ፒፓ ተዋስኩኝና እዚህ ላይ (ደረት ኪሳቸው) ላይ አገባሁኝ። እዚህ ኪሴ ውስጥ ያንን ፒፓ አደረኩ፤ አንድ ከቻይና የመጣ ባለ ግላስ ኮት ገዝቼ ነበር። ከዛ በኋላ አነስተኛ የመኪና ረዳትና ደላሎች ያሉበት ከረንቡላ ቤት ገባሁኝ። ገና ስገባ በስድብ፣ የአካባቢ ስድብ፣ አስቀድሜ (የወቅቱን ስድብ እሳደባለሁ) አስራ አምስት ቀን እራሴን አጣጥል ነበር። ያን ይገፔ ገባሁ ጓደኞቼ በሙሉ ሲታሠሩ እኔ በኋላ ነው የታሠርኩት *እሡ ተራማጅ ነው* አሉ። *ሰካራም ሆኗል* አሉ። *አጫሽ ሆኗል።* ልብሱ ሁሉ የእንትን ነው ተባለልኝ። በዚህ የተነሳ ለአንድ ለሁለት አመት ያህል አመለጥኩኝ። በኋላ ግን ታሠርኩ፤ በእውነት በ17 አመቱ ውስጥ ስራ አልሠራሁም። ምክንያቱም ምን ነበረ? ያመረትነው የሠራነው ቡና በእኛ ግዜ ሀያ ብር ሀያ አንድ ብር የሚሸጠው ደርግ ሲመጣ 150 ብር ገባ። እና በዚህ አይነት ጥቅም ሲኖሩ እንደው ላለመጠመድ … እኔ እርግጥ መንግስቱን እጠላ ነበር። ያለፈው ነገር ምን ያደርጋል? ከዚህ በኋላ ደርግ እንደወጣ ኢህአዴግ እንደገባ ዩኒቨርስቲ አዳራሽ ውስጥ ከዕድሜዬ 17 ዓመት ቀንሺያለሁ፤ 17 ዓመት ያልሠራሁበት ስለሆነ ከዕድሜዬ መቀነስ አለበት ብዬ ኢህአዴግ ከገባ ነው ስራ የጀመርኩት። በዛን ግዜ እራሴን ችላ የምልበት ነበር እንጂ በደርግ ጊዜ ሥራ አልሠራሁም። አሁን ላለሁበት ሥራ እንግዲህ ኢህአዴግ ከገባ ፋብሪካ ... ታምራት ላይኔ 200 ሚሊዮን የወጣበት የበደሌ ቢራ ፋብሪካ ያለ ምንም ሥራ ቁጭ አለ ... በእውነት ፈታኝ ጊዜ ነው። ምሪቱን የሚያከፋፍል ሰው ሲፈለግ አቶ ተከስተ የፋይናንስ ምክትል በኢህአዲግ ፅህፈት ቤት የነበረ እኔ አንድ ሰው አይቻለሁ አቶ ተካን እንሞክረው አለ። ገንዘብ የለኝ፣ ምን የለኝ። ለ400 ኪ.ሜ መጓጓዣ መኪና የለ፣ ገንዘብ ያለ፣ ጠርሙስ የለ፣ ምንም የለም። እዚህ ከተማ ከነጋዴዎች ጠርሙስ ስጡኝ ብዬ 22 ሺ ሣጥን ሠጡኝ። በቃ በዛ ያ ፋብሪካ በአንድ ጊዜ ተነሳ ለትልቅ ደረጃ ደረሠ፤ በዛ ስራ ጀመርኩኝ። እና ምንም ወደኋላ አላልኩም፤ ደርግም ለወሠደብኝ ሀብት ብዙም አልተጨነኩም። ከዛ በኋላ እንደገና የቻይና ወኪል በመሆን ከመንግስትም ፈላልጌ ጠቅላላው ኦቶብስ አስመጭነት ሥራ ጀመርኩ። ከቻይና ጋር መስራት አይቻልም። ሁለቱም በክርን ደቆሱኝ። በደሌ ቢራ 15 ሚሊዮን ብር አውጥቼ ካፈሰስኩ በኋላ፣

ቻይኖችም መና አስቀሩኝ በእውነት በጥረት፣ በብርታት፣ ተስፋ ባለ መቁረጥ አሁን ያያችሁት ፋብሪካ ለኢትዮጵያ አይደለም፣ ለአፍሪካ የመጀመሪያ ነው፡፡ በምን አገኘሽው፣ በምን አወጣሽው ይሄ ቴክኖሎጅ አይወጣም ይላሉ፡፡ በብዙ ጥረት በብዙ ልፋት ነው፡፡ እና በደርግ ግዜ አልሠራሁም፤ የሠራሁት አሁን ነው፡፡

መቼም አርግጥ ሠው እንደ ፀባዩ ነው፡፡ እርግጥ ድህነት ጥሩ ነው ይቻላል፡፡ ድህነት እራሱ አስተካክሎ ይሠጣል ለሠው ልጅ መሄጃውን፡፡ ገንዘብ ማግኘት ደግሞ መቻል አለበት፡፡ ገንዘብ ማግኘት የቻለ ትልቅነት ነው፡፡ እርግጥ ስራን መስራት፣ ማስፋፋት ያስፈልጋል ለማንም ቢሆን፡፡ የሀገራችን የድሮ ነጋዴ ሲነሳ መንገድ ዝግ ነው፤ ከእናትህ ሆድ የወጣህ ያህል ነው፣ ጨለማ ነው፡፡ ዛሬ ኢንተርኔት አለ፤ ቴሌቪዥን፤ አለ፤ ሬዲዮ አለ፤ የአለም መጓጓዣ አውሮኘላን አለ፤ አስበው እስቲ ሁሉ ነገር አለ፡፡ ደግሞ እውነት እላችኋላሁ እኔ የተቀጠርኩት አንድ ቀን ነው፡፡ በዛሬው ቀን እንኳን ከ200 በላይ ሠራተኞች አሉኝ፣ ጥሩ ደመወዝ የሚበሉ አሉኝ፡፡ እስካሁን ድረስ በስራ ላይ አለሁ፡፡ እርግጥ በደሌ ቢራ ብዙ ጉዳት አደረሠብኝ፤ ቻይናም እንዲሁ፡፡ ነገር ግን በኋላ ረድተውኝ ነው ቴክኖሎጅውን ላመጣ የቻልኩት፡፡ እዚህ ላይ ጉብዝና ፋብሪካ መትከል ብቻ አይደለም፡፡ ጉብዝናው ቴክኖሎጅ ማስገባቱ ላይ ነው አንዱ ቻይናዊ ስለቀለም ሊጠይቅ ፋብሪካው ኢትዮጵያ አይደለም አፍሪካም አልገባም፤ ወደፊት ይገባል፤ ቀለሙ አይገኝም አለኝ፡፡ እርግጥ ይሄ አሁን የምታዩት ፋብሪካ ሌላ ሀገር አልገባም፡፡ አሁን እኔ ካመጣሁ በኋላ ብዙ ሠዎች ይሯሯጣሉ፡፡ ስለዚህ መስራት መውደቅ ማደግ፤ ሰው ከሠራ ሁልግዜም እንደዚህ ነው፡፡

**ጥያቄ፡-** በተፈጥሮ ያላቸው የኢንተርኘሩነር እውቀት ተምረውም ዩኒቨርሲቲ ተገብቶም የማይገኝ ነው፡፡ እኔ ስለሰማሁት ሌሎች ጓደኞቼ ስላልሠሙት በጣም ነው የምቆጭበት፡፡ ድህነት ቅነሳ ማለት ስራ ፈጣሪነት ነው ይሄን መድረክ ያዘጋጀው ማኅበራዊ ጥናት መድረክን እያመሠገንኩኝ ሠፋ ባለ ሁኔታ በተለይም ለወጣቱ ክፍል በተቻለ መጠን አንዴ ቢቀርቡ ወጣት ስራ ፈጣሪነትን ቢለምድ ድህነት ቅነሣን ከማገዝ አኳያ ትልቅ አስተፅዎ ይኖረዋል እላሁ፡፡ በእውነት እጅግ በጣም ነው የማመሠግነው፡፡ ሌላ መጠየቅ የምፈልገው ጥያቄ ከጠንካራ ወንዶች ወይም ውጤታማ ከሆኑ ወንዶች በስተጀርባ ጠንካራ ሴቶች አሉ ይባላል እና ምናልባት ስለባለቤትዎ አስተዋጽዎ እንደው ትንሽም ቢሆን ቢገልፁልን ደስ ይለናል፡፡

**ቀኛዝማች፡ -** ጉበዝ ነች፡፡ ጉብዝናዋ ምንድን ነው የእኔን ጠባይ ችላ መኖሯ ነው ለዚህም በጣም አመሰግናታለሁ፡፡ እናንተም ልታመሰግኗት ይገባል፡፡ የእኔ ጠባዬ ምንድን ነው ሳይቸግረኝ ሌሊት ተነስቼ እሰራለሁ ዛሬ የአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ ምንድን ነው፣ ምን ያገኛል፣ ምን ይበላል፤ ምን ይጠጣል እላለሁ፡፡ ስሰራ ሳብድ ነው የማድረው፡፡ ያን ሁሉ ፀባይ ችላ መቆየትዋ ጉብዝና ነው፡፡ ድሮም ስንጀምር በእርግጥ ጉበዝ ነበረች፡፡ ስንጀምር እንጀራ ሁሉ እየጋገረች ከመጨረሻ ድህነት ነው የተነሳነው፡፡ እኔ አሁን ስለ አነሳሴ አቶ መኰንን ጫፍ ጫፉን ነው የነገረን፡፡ እኔ ከመጨረሻው ደረጃ ነው የተነሳሁት፡፡ ስንጀምር የከሰል የቡና ማሽን ነበረ፡፡ እግዚአብሄርም ደግሞ አሁን ሳየው ደግ ነው፡፡ ከሠል ሠው ይገድላል፤ ያፍናል፤ ምንትሴ ይባላል፡፡ አንድ ኩንታል ከሠል ማሽን ስናቀጣጥል እናድራለን፡፡ ሆቴል ነበረን፤ ጋጋሪ ሲጠፋ ሁለት ምጣድ ይዛ ስታቦካ ስትጋግር ነበር፡፡ እና በኋላ እርግጥ ከኔ ጋር ውጭ የወጣው ስራ አለ፡፡ እኔ የቀዳማዊ ሐይለ ሥላሴ የሽልማት ድርጅት የመጀመሪያ ተሸላሚ ነኝ፡፡ ኢትዮጵያን በእርሻ የአለም ባንክ የታለ የሰራችሁት ሲል አምጥተው ያሳዮ ነበር የኢትዮጵያን ቡና ከ51 ሺህ ቶን ወደ 84 ሺህ ቶን አድርሰናል፡፡ ኬኔዲ ጆን ፓል ከእኛ ጋር ነበሩ፡፡ የኦክላሆማ ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት ጭምር መጥቶ ሥራችንን ጉብኝቷል፡፡ ይሄንን ያደረኩት ብዙ ለፍቼ ነው፡፡ ከንግድ ስራዬ ወደ እርሻ ቦታ እሄዳለሁ፤ 12 ሰአት ሉቅ ሲዘጋ ወደ እርሻ ቦታ እሄዳለሁ፡፡ ከምሽቱ 3 ሰአት 4 ሰአት እመለሣለሁ፡፡ ጧት ተነስቼ 10 ሰአት ሲሆን እንደገና እሄዳልሁ፡፡ እንደዚህ ሆኜ ነው በእርሻ ስራ ላይ ተሠማርቼ እርሻ ሆኜ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያው ተሸላሚ ለመሆን የቻልኩት፡፡ እኔ በጣም አልቀብጥም፡፡ እቤት አልውልም፡፡ ጓደኞቼ ነጭ ልብስ ለብሠው ምናምን እንኳን ሲሉ እኔ ጭቃ ላይ ውዬ ስመለስ ያንን ችላ ባለቤቴ በመቀመጥ እስከዛሬ ድረስ አለች፡፡

***

**የማኅበራዊ ጥናት መድረክ**

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) አትራፊ ያልሆነ፣ ልማት-ነክ በሆኑ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ጥናት የሚያካሂድ ነፃ ተቋም ነው፡፡ ማጥመ በሕዝባዊ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ነፃ የውይይት መድረኮችን ያዘጋጃል፤ የሕዝብን ግንዛቤ ለማዳበር ይንቀሳቀሳል፡፡ በፖሊሲ ክርክሮች ውስጥ ሰፋ ያለ የሕዝብ ተሳትፎን ማዳበር ለዲሞክራሲው ሂደት ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ብሎ ማጥመ ያምናል፡፡ ግቦቹን ለማሳካትም ማጥመ ዐውደ-ጥናቶችን ያዘጋጃል፣ የምርምር ውጤቶቹንም በማሳተም ለፖሊሲ አመንጪዎችና ሌሎች የመንግሥት አካላት፣ ለሲቪል ማኅበራት፣ ለባለሙያዎች፣ ለግሉ ክፍለ-ኤኮኖሚ አባላትና ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ እንዲሁም ለለጋሽ ድርጅቶች ያሠራጫል፡፡